***Haramaya Law Review, Vol.*** 10 (2021) ISSN: 2227-2178 (P) & 2305-3739 (E)

**To cite this article:** *አልዩ አባተ ይማም, አመክንዮአዊ የሸሪዓ ሕግ ምርምር (ኢጅቲሓድ)፡- ዘዴው፣ እርከኖቹ እና ዘመነኛ እድገቶቹ*, HARAMAYA LAW REVIEW 10: 85-102 (2021)

# አመክንዮአዊ የሸሪዓ ሕግ ምርምር (ኢጅቲሓድ)፡- ዘዴው፣ እርከኖቹ እና ዘመነኛ እድገቶቹ

*አልዩ አባተ ይማም*

## Abstract

*Sharia has three main sources: the first two, Quran and Sunnah, constitute a transmitted or revealed sources of knowledge whose rules and principles are deduced from traditions. The third source of Sharia is rational thinking referred to in the Sharia literature as Ijtihad. The first two revealed sources of the Sharia have a generalist feature whereby their content is dominated by broad principles of law and objectives of law, leaving the wider corpus of specific rules to be covered by independent reasoning of scholars. This approach of the Sharia aims at enabling the Sharia to be amenable to changing realities of a society through the instrumentality of Ijtihad. While the introductory literature of Ijtihad provides basic explanation of its meaning and characteristics as a source of Sharia, this paper, perhaps being the first Amharic work on the topic, delves into technical aspects of independent Sharia reasoning, which includes governing principles, methodology and requirements for the proper practices of Ijtihad as developed by Sharia jurists (Mujtahids) of early and contemporary periods. In relation to the interpretation and application of Sharia in Ethiopia on personal matters and, recently, on interest free financial transactions, it is definitely very important for Sharia courts, practitioners and regulators of Islamic finances to acquaint themselves with the methodology of Ijtihad to ensure flexibility in the understanding and application of relevant Sharia laws and realize that all juristic and scholarly exercises of Ijtihad is directed towards the fulfillment of Sharia objectives (Maqasid) at all levels.*

## ሀ. መግቢያ

ሸሪዓዊ የሕግ ምርምር *(ኢጅቲሓድ)* ሦስተኛው የሸሪዓ ምንጭ መሆኑን እና ዝርዝር የሸሪዓ ሕግጋትን በመቅረጽ ረገድ ሰፊ ድርሻ ያለው ከመሆኑ አንጻር ምንነቱን፣ ንድፈ-ሐሳቦቹን፣ የምርምር ዘዴዎቹንና ሥነ-ሥርዓት እንዲሁም ሌሎች በርዕሱ ሥር የሚነሱ መሠረታዊ ፍሬ-ሐሳቦችንና ጭብጦችን የሚዳስስ ጽሑፍ ለኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ያለው አግባብነትና ጠቀሜታ ምንድን ነው የሚል ጥያቄ በአንባቢው በኩል ሊነሳ ይችላል፡፡ ለዚህ ምላሹ ደግሞ ከኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት አንቀጾች የሚገኝ ነዉ፡፡[1] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 34 (5) እና 78 (5) ላይ እንደተደነገገዉ ከኦፌሴላዊ የመንግሥት የሕግና ፍትሕ ሥርዓት በተጓዳኝ እውቅና ሊሰጣቸው የሚችሉ የሕግ ሥርዓቶች አሉ፡፡ እነሱም ባህላዊና ሃይማኖታዊ ሕጎች ናቸው፡፡ በሕብረተሰቡ ውስጥ የሚነሱ ግላዊና የቤተሰብ ግጭቶች በባለጉዳዮቹ ፈቃድ በባህል ወይም በሃይማኖት ሕጎች መሠረት ሊዳኙና እልባት ሊሰጣቸው እንደሚችል ሕገ-መንግሥቱ ያስቀምጣል፡፡

* ኤል.ኤል.ኤም. በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በሕግ እጩ ዶክተር፣ ጸሐፊውን በኢ-ሜይል አድራሻ alyuabate09@gmail.com ማግኘት ይቻላል፡፡

[1] የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት፣ አዋጅ ቁጥር 1/1987፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 1ኛ ዓመት ቁጥር 1፣ 1995፣ አንቀጽ 34(5) እና 78(5)፡፡

ተቋማዊ አደረጃጀቱን በተመለከተ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 78(5) ላይ እንደተመለከተው የግልና የቤተሰብ ግጭቶችን የመዳኘት ሥልጣን ያላቸው ሃይማኖታዊና ባህላዊ ፍ/ቤቶችን የማቋቋም ሥልጣን በፌዴራል ደረጃ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሁም በክልሎች ደረጃ ለክልል ምክር-ቤቶች ተሰጥቷል፡፡ በዚህ የሕገ-መንግሥት ድንጋጌ መሠረት የባህልና የሐይማኖት ፍ/ቤቶችን የማቋቋም ጥያቄዎችን ተቀብሎና ገምግሞ በቂ ፍላጎት ያለና አስፈላጊነቱ የታመነበት ከሆነ በሕግ አውጪዎቹ ይሁንታ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች ተቋቁመው የሕግ ብዝኃነቱ አካልና ተዋናይ እንዲሆኑ ሊደረጉ እንደሚችል መረዳት ይቻላል፡፡ እንደ እድል ሆኖ ከመደበኛ ፍ/ቤቶች ውጪ ያሉ የዳኝነት አካላት የሚቋቋሙበት ይህ ሥርዓት ለሸሪዓ ፍ/ቤቶች ተፈጻሚ አይሆንም፡፡ እንዴት ከተባለ ምላሹ በህገ-መንግስቱ አንቀጽ78(5) ላይ ይገኛል፡፡ ይሄውም ሕገ-መንግሥቱ ከመጽደቁ በፊት በመንግሥት እውቅና አግኝተው ሲሰራባቸው የነበሩ የባህል ወይም የሃይማኖት ፍ/ቤቶች እውቅና አግኝተው እንዲደራጁ የሚያስገድድ በመሆኑ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ታሪክ ደግሞ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ከአጼ ኃይለሥላሴ ሥርዓተ-መንግሥት በፊት ጀምሮ በሥራ ላይ የነበሩ በመሆኑ[2] በንጉሱ ዘመን ደግሞ የቃዲና የናኢባ ፍ/ቤቶች ተብለው በ1934 እና በ1936 በወጡ የማቋቋሚያና የማሻሻያ አዋጆች ተደራጅተው ሲሰሩ የነበሩ ናቸው፡፡[3] ስለሆነም ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ከመንግሥታዊ የዳኝነት ተቋማት በተጓዳኝ በመሥራት ከሕገ-መንግሥቱ መጽደቅ በፊት ሲሠሩ የነበሩ በመሆኑ እነዚህን ፍ/ቤቶች በፌዴራልና በክልል ደረጃ አቋቋሞ ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ማድረግ በሕግ አውጪዎች ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ሕገ-መንግሥቱ ራሱ ያቋቋማቸው እና እውቅና ማግኘታቸው በሕግ አውጪ አካላት ላይ የተጣለ ሕገ-መንግሥታዊ ግዴታ መሆኑን ይገነዘቧል፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ‹የፌዴራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ቁጥር 188/1992 በተሰኘ አዋጅ አማካይነት ፍ/ቤቶቹ በይበልጥ ተጠናክረውና ተደራጅተው እየሰሩ መሆናቸው የታወቀ ነው፡፡ በተመሳሳይ የክልል መንግሥታትም በበኩላቸው ክልላዊ ተፈጻሚነት ያላቸው የየራሳቸውን የሸሪዓ ፍ/ቤቶች ማጠናከሪያ አዋጆች አውጥተው በሃገሪቱ ዙሪያ በወረዳ፣ በዞንና በክልል ደረጃ፣ የመጀመሪያ፣ ከፍተኛና ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ተደራጅተው በተከራካሪዎች ፈቃድ ላይ ተመርኩዘው በግልና በቤተሰብ ጉዳዮች ላይ ሸሪዓዊ ፍትሕን በማድረስ ላይ እንደሚገኙ ይታወቃል፡፡ ይህም ሕጋዊ እውቅና ያገኘ የሕግ ብዝኃነት (*Legal Pluralism*) የሃገሪቱ የሕግ ሥርዓት አካል እንደሰፈነ የሚያሳይ እውነታ ነው፡፡[4]

በፌዴራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ማጠናከሪያ አዋጅ አንቀጽ 3 መሠረት ለሸሪዓ ፍ/ቤቶች የሚቀርቡ ጉዳዮች በሸሪዓ ሕግ መሠረት እንደሚዳኙ ይደነግጋል፡፡ የሸሪዓ ሕግ ደግሞ በጥቅሉ ሁለት ምንጮች አሉት፡፡ እነሱም ራዕያዊ *(ነቅሊያሕ/revealed)* እና አመክንዮአዊ *(ዐቅሊያሕ/rational*) ምንጮች ናቸው፡፡ ራዕያዊ ምንጮች በመለኮታዊ ራዕይ *(ወህይ)* የተገለጹ ሲሆኑ ቁርአን እና *ሱናሕ* በዚህ ምድብ ስር ይወድቃሉ፡፡[5] በአመክንዮአዊ የሸሪዓ ምንጮች ስር ደግሞ በ*መዛሒብ* (የሕግ ት/ቤቶች) መስራቾችና (*ኢማም/አኢማሕ*) እና የ*ኡሱል አል-ፊቅሕ* (የሸሪዓ መሠረተ-ሐሳቦች)

---

[2] Mohammed Abdo, *Legal Pluralism, Sharia Courts, and Constitutional Issues in Ethiopia*, 5(1) MIZAN LAW REVIEW, 78 (Spring 2011). ዛኪ ሙስጠፋ፣ *በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙት የእስላም ፍርድ ቤቶች የሚሰራበት ሕግ፤ ለሸሪዓ ሕግ በሥራ ላይ መዋልና መቀጠል ምክንያት የሆኑ ነገሮች*፣ 9(1) Journal of Ethiopian Laws, 173(1965.

[3] የቃዲ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ፣ ቁጥር 2/1934 እና የቃዲዎችና የናኢባ ምክር-ቤቶች አዋጅ ቁጥር 62/1936፡፡

[4] በሕግ እውቅና ካገኘ የሕግ ብዝኃነት (De-jure) በተቃራኒ ሕግ የማይፈቅደውና እውቅና ያልተሰጠው የፍሬ-ነገር የሕግ ብዝኃነት (De-facto) አለ፡፡ ይህ የብዝኃነት ጽንሰ-ሐሳብ በአንድ የሕግ ሥርዓት ውስጥ በተጨባጭ የሚታየውን ከመንግሥታዊ የፍትሕ ሥርዓት በተጓዳኝ የግለሰቦችንና የማህበረሰብ ባህርይ እና ምግባር የሚቀርጹና የሚመሩ ሕጎች ተግባራዊ የሚሆኑበትን ነባራዊ እውነታ የሚያመለክት ነው፡፡ ለምሳሌ በኢትዮጵያ የሸሪዓ ሕግ ወይም ባህላዊ ሕጎች በባህላዊ እና ሃይማኖታዊ የፍትሕ ተቋማት አማካይነት ከተፈቀዱበት ወሰን አልፈው በፍትሐ-ብሔራዊ በንግድ እና በወንጀል ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ የሚደረጉ መሆኑ የማይካድ ሃቅ ነው፡፡ ከሕግ እውቅና ውጪ የሆነው ነባራዊ ብዝኃነት በሃገራዊ የፍትሕ ሥርዓት በጾታ እኩልነት እና የሰብዓዊ መብት በልማታዊ የፖሊሲ አፈጻጸም እርምጃዎች ላይ የራሱ የሆኑ አሉታዊ ሚናዎች ያሉት ሲሆን ለባህላዊና የሃይማኖት የሕግ ሥርዓቶች የተሰጣቸው የእውቅና ደረጃና የተፈጻሚነት ወሰን የተወሰነው ግጭቶችን ለመፍታት ካላቸው ውጤታማነት (Instrumental Function) በሰብዓዊ መብቶች በእድገትና ሥልጣኔ ለይ የሚጋርጧቸው ችግሮች እና ሌሎች ታሳቢዎች ግምት ውስጥ ገብተው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከነዚህ እሳቤዎች አንጻር ደጋፊ ወይም ነቃፊ የመከራከሪያ ሐሳቦች ሊቀርቡ የሚችሉ መሆኑ እና እየቀረቡ ያሉ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

[5] Ahmad Hasan, *The Sources of "Fiqh": A General Survey*, 29(2) ISLAMIC STUDIES, 114 (Summer 1990) በራዕያዊ የሸሪዓ ምንጮች ማለትም በቁርአንና ሱናሕ የሕግ ምንጭነት ምንነትና መገለጫዎች ላይ ማብራሪያ ለማግኘት አልዩ አባተ ይማም፣ ቀዳሚው የሸሪዓ ሕግ ምንጭ፣ 2 HAWASSA UNIVERSITY JOURNAL OF LAW (July, 2018), እንዲሁም አልዩ አባተ ይማም፣ ሱናሕ፡- ሁለተኛው የሸሪዓ ሕግ ምንጭ፣ 3 HAWASSA UNIVERSITY JOURNAL OF LAW, (July, 2019) ያንብቡ፡፡

ሊቃውንት የተቀረጹ ለሕግ ምርምር *(ኢጅቲሓድ)* መንደርደሪያና ለዝርዝር ሕጎች ምንጭ የሆኑ ጥቅል የሕግ መርሆዎች ይገኛሉ። ከእነዚህ የ*ኢጅቲሓድ* መርሆዎች መካከል ምስስሏዊ አመክንዮ *(ቂያስ/analogy)*፣ የሕዝብ ጥቅም *(መስላሃሕ/Public Interest)፣* ከምንጩ ማድረቅ (*ሰድ አዝ-ዘራኢዕ/* Blocking the Means)፣ ርትዕ *(ኢስቲህሳን/Equity)* ወዘተ.. ይገኙበታል።[6]

የዚህ ጽሁፍ ዓላማ እነዚህን *የኢጅቲሓድ* ንድፈ-ሐሳቦች መተንተን ሳይሆን[7] አመክንዮኣዊ ሸሪዓ ምርምር ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ በሊቃውንት የዳበሩ ዘዴያዊ መርሆዎችና የአፈጻጸም *ሥነ-ሥርዓት* እና የምርምር እርከኖችን ማብራራት ነው። በተጨማሪም በ*ኢጅቲሓድ* ከጥንት በሸሪዓ የሕግ ት/ቤቶች እና ሊቃውንት *(ሙጅተሒዱን)* የነበረው እድገት እንደተጠበቀ ሆኖ ከ19ኛው ክ/ዘመን ወዲህ ምሁራዊ የእሳቤ ንቅናቄና ተሃድሶ በተመዘገበባቸው ባለፉት ሁለት ምዕተ-ዓመታት ውስጥ የታዩ ቁልፍ እድገቶች ያስቃኛል።

## ለ. የኢጅቲሓድ ዘዴ እና *ሥነ-ሥርዓት*

በሸሪዓ ሕግ እድገት ውስጥ *ኢጅቲሓድ*ን የሚመሩ መርሆዎችን መዘርጋት ያስፈለገበትን ጊዜ ስናይ ከነቢዩ ሕልፈት በኋላ ባልደረቦቻቸው *(ሶሃቢዩን)* ለአንድ ጉዳይ ሸሪዓዊ መፍትሔ ለመስጠት በቀጥታ ከምንጮች ያጣቅሱ እንደነበርና እንዲሁም የሕብረተሰብ ጥቅም *(መስላሃሕን)* መሠረት ያደርጉ እንደነበር የሸሪዓ የሕግ *ታሪክ* ያስረዳል። በዚህ የምንጮች የሕግ አወሳሰድ እና *መስለሃሕን* ግምት ውስጥ በማስገባት ረገድ ከግላዊ *ኢጅቲሓድ* ይልቅ በምክክር *(ሹራ)* ወይም በባልደረቦች የ*ጋራ* ምክክር (*ኢጅማዕ)* አማካይነት ቀዳሚና ሰፊ ድርሻ ነበረው። ከባልደረቦች በኋላ የመጣው የተከታዮች *(ታቢዑን)* ትውልድ የነበረውን *የሶሃቢዎች* አሻራ ያስቀጠሉ እና በተለይ ደግሞ በኡመያድ አገዛዝ ወቅት የሙስሊም የግዛት መስፋፋት ተከትሎ የውጪ አገዛዞች ከነበራቸው ተጽእኖ እና የተለያየ እሳቤ ያላቸው ቡድኖችና አንጃዎች እንዲሁም ምሁራዊ ብቃታቸው አጠያያቂ የሆኑና ግላዊ እይታ የሚያንጸባርቁ ግለሰቦች በመነሳታቸው ምክንያት የሙስሊሞች አንድነትና የሸሪዓ ተዓማኒነት አደ*ጋ* ላይ በመውደቁ የተነሳ ከቀዳሚ ምንጮችና ተጨባጭ እውነታዎች ላይ በመመርኮዝ የሚደረግ ማንኛውም ምርምር *(ኢጅቲሓድ)* ራሱን የቻለ ዘዴና መመሪያ ሊበጅለት እንደሚገባ የዘመኑ *ዑለማእ* ያመኑበት በመሆኑ *ሥነ-ሥርዓቱ*ን የሚዘረጉ ሐሳቦች በምሁራን መካከል መንሸራሸር እና የድርሰናቶቻቸውም ዋነኛ ትኩረት ለመሆን ችለዋል።[8]

የ*ኢጅቲሓድ* መርሆዎችን በመለየት ምሁራዊ ጥረት ላይ ተቃውሟቸውን በመግለጽ ለየትኛውም ጥያቄ ምላሹን በቁርአን ወይም በ*ሀዲስ* ውስጥ ከመፈለግ ባሻገር ሌላ ምክንያታዊ የሕግ ምርምርን ያወግዙ የነበሩ *የሀዲስ* አራማጆች *(አሕል አል-ሀዲስ)* የተሰኘ የሊቃውንት ስብስብ ተነስተው የነበረ ቢሆንም በተቃራኒው ደግሞ እንደ ሀነፊዎች ያሉ *አሕል አር-ራእይ* (የእሳቤ/አመክንዮ አራማጆች) ደግሞ ለዘመን አመጣሽ ጥያቄዎች በምንጮች ቀጥተኛ ሽፋን ያላገኙ ሲሆን አመክንዮን እና ዓላማን መሠረት ያደረገ ምርምር ማድረግን መርጠዋል፤ በውጤቱም *ለኡሱል አል-ፊቅሕ* እድገት መሠረቱን ጥለዋል።[9]

ከ*ኢጅቲሓድ* ዘዴዎች/መርሆዎች መካከል ቀዳሚውና በሀነ*ፊ መዝሓብ* የተለየው መርሆ *ቂያስ* (ምስስሏዊ አመክንዮ) ነበር። *ቂያስ* ማለት አንድ ቀድሞ የወጣ ሕግ የተደነገገበትን ምክንያት *(ዒላሕ)* በመለየት ተመሳሳይ ምክንያት ተፈጻሚ ለሚደረግባቸው አዳዲስ ጥያቄዎች ላይ ነባር ድንጋጌ ገዢ እና ተፈጻሚ እንዲሆን የማድረግ ዘዴ ነው። በሌላ አገላለጽ አዲሶቹ ጭብጦች ቀድመው በቁርአን ወይም በ*ሱናሕ* ውስጥ ከተካተቱት ሕግ*ጋ*ት የድን*ጋ*ጌ ምክንያት *(ዒላሕ) ጋ*ር የሚመሳሰል ከሆነ ሕጉ አዲሶቹን ጉዳዮችንም እንዲሸፍን ማድረግ ነው። ለምሳሌ በ*ሀዲስ* እንደተደነገገው ሟችን የገደለ ወራሽ ከወራሽነቱ ይነቀላል፤ የዚህ ድን*ጋ*ጌ *ዒላሕ* አንድ ወራሽ በፈጸመው ወንጀል ድርጊት ሊቀጣ እንጂ ተጠቃሚ ሊሆን አይገባም የሚል ሐሳብ ያዘለ ነው። ድን*ጋ*ጌው የሕግ (የዝምድና) ወራሾችን የሚመለከት በመሆኑ አንድ ኑዛዜ ተቀባይ ኑዛዜ ሰጪውን የገደለ እንደሆነ ከውርሱ መካፈል ይችላልን ለሚለው *ፈርዕ*

---

[6] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 115.

[7] በኢጅቲሓድ ምንነት፣ መገለጫዎች እና ሸሪዓዊ የምንጭነት ድርሻ ላይ መሠረታዊ ግንዛቤ ለመጨበጥ፣ አልዩ አባተ ይማም፣ ሦስተኛው የሸሪዓ ምንጭ፣ አመክንዮኣዊ የሕግ ምርምር (ኢጅቲሓድ):- ምንነቱና መገለጫዎቹ፣ JIMMA UNIVERSITY JOURNAL OF LAW, Vol. 11, December 2019. ይመለከቷል።

[8] MOHAMMAD HASHIM KAMALI, SHARIA LAW: AN INTRODUCTION, 166 (Oxford፡ Oneworld Publications, 2008).

[9] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 167.

(ልዩ ጭብጥ) ለሕግ ወራሾች ተፈጻሚ የሚሆነው የ*ሱናሕ* ደንጋጌ በተመሳሳይ ለኑዛዜ ወራሾችም ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል፤ የ*ሀዲስ* ድንጋጌ *ዒላሕ* ለአዲስ ጭብጥም ቀጥተኛ አግባብነት ያለው በመሆኑ ነው፡፡

በ*ቂያስ* አጠቃቀም ላይ አከራካሪ የነበረው የሕጎችን ድንጋጌ ምክንያት *(ዒላሕ)* መለየት ላይ ነበር:: በተለይ ደግሞ በነባሩ ሕግ የተለየው *ዒላሕ* ከአዲሱ ጉዳይ ጋር ተመሳሳይነት ብቻ ያለውን እና አንድ አይነት የሚባል ባልሆነ ጊዜ ይበልጥ አወዛጋቢ ይሆናል፡፡ አንድን ድንጋጌ ለአንድ ዓይነት ጉዳዮች ተፋጻሚ ማድረግ የሚያስነቅፍ ባይሆንም አንድን ድንጋጌ አንድ ላልሆኑ ግን ተመሳሳይነት ላላቸው ጉዳዮች ተፋጻሚ ማድረግ አንዳንድ ጊዜ ያልተፈለገ ውጤትን ሊያስከትል ስለሚችል ለዚህ መፍትሔ ይሆን ዘንድ የሀነፊ *መዝሓብ* ሌላ የ*ኢጅቲሓድ* መርሆ ለመቅረጽ ተገደዋል፤ ይኸውም *ኢስቲህሳን (ርትዕ)* ነው፡፡[10] በ*ኢስቲህሳን* የሕግ ፍልስፍና መሠረት አንድን ድንጋጌ ለተመሳሳይ ጉዳዮች ተፋጻሚ ማድረግ ተገቢ ቢሆንም እንደ ጉዳዮቹ ልዩ ሁኔታ ግን ሕጉን ተፈጻሚ ማድረግ አስከፊ ውጤትን የሚፈጥር እና የሕጉንም ዓላማ የማያሳካ ሲሆን በርትዕ እሳቤነት የሕጉ አፈጻጸም ቅርጽ ሊቀየር ይችላል የሚል ጽንሰ-ሐሳብ ያዘለ ነው፡፡[11] በሌላ በኩል አሽ-ሻፊዒ የ*ቂያስ* ቀንደኛ ደጋፊ ቢሆኑም፣ *ኢስቲህሳንን* ግን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርገውታል፡፡ ለዚህም ምክንያታቸው ሕግ በርትዕ ስም እንዳይፈጸም የሚደረግ ወይም አፈጻጸሙ የሚለወጥ ከሆነ ሕግ ለግላዊ አስተያየት ተገዢ እንዲሆንና ለዘፈቀደኝነት ተጋላጭ እንዲሆን የሚያደርገው በመሆኑ ነው፡፡ የሻፊዒ ነቀፌታ ሕግ ቢወጣም ዋናው አተረጓጎሙና አፈጻጸሙ ነው የሚያስብል አፍራሽ *ሥርዓትን* ይዘረጋል ከሚል *ሥጋት* የመነጨ ነው፡፡[12]

ሌላዉ *የኢጅቲሓድ* መነሻ መርሆ ‹የሕዝብን ጥቅም ማስቀደም *(ኢስቲስላሕ/መስለሃሕ)*› ነው፡፡ ይህን የእሳቤ መስመር ግንባር-ቀደም የሚባሉት የሸሪዓ ሕግ ት/ቤቶች የተቀበሉት ቢሆንም በቀዳሚ ምንጮች ውስጥ ያሉ የሸሪዓ ሕጎችን በመተርጎምም ሆነ አዲስ ሕጎችን በመቅረጽ ረገድ መርሁን ያለገደብ የተቀበሉትና ተግባራዊ ያደረጉት *ኢማም* ማሊክ በመሆናቸው የ*መስለሃሕ* ንደፈ-ሐሳብ ባለቤት የማሊኪ ት/ቤት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡[13] የማሊኪዎች ሌላው አበርክቶ *ሰድ አዝ-ዘራኢዕ* (ከምንጩ ማድረቅ) ነው፤ በዚህ የሕግ ንድፈ-ሐሳብ መሰረት ሕጋዊ ድርጊትን በመታከክ ሕገ-ወጥ ውጤትን ለማስገኘት የሚደረግ አካሄድን ማስወገድ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ በሕግ ስም ሕገ-ወጥ ውጤት ወይም ጥቅም ለማስግኘት የሚከፈትን በር ቀድሞ መዝጋት ገና ውጤቱ ግዙፋዊ ሳይሆን በእንጭጩ መቅጨት ማለት ነው፡፡[14]

የሻፊዒ ት/ቤት ደግሞ የ*ኢስቲሰሃብ* (የቀጣይነት ግምት) የሕግ መርሆን አበርክቷል፡፡ በዚህ ንድፈ-ሐሳብ መሠረት ሕግ አመክንዮና ፍሬ-ነገሮች መለወጣቸው እስካልተረጋገጠ ድረስ ጸንተው እንዳሉ ይቆጠራል የሚል ነው፡፡[15] *ኢስቲስሃብ* ለውጥ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የነበረው እንዳለና እንደቀጠለ ይቆጠራል በማለት ሕግና የፍርድ ውሳኔዎች በብዛኃኑ ዘንድ ተገማች እንዲሆኑ ያስችላል፡፡ ለምሳሌ ያህል እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር ግምት በጥፋተኝነት ማስረጃ እስካልተሻረ ድረስ ሁልጊዜም እንዳለ የሚገመት ነው፡፡ በተጨማሪም ፍቁድነት *(ኢባሀሕ)* ጽንሰ-ሐሳባዊ መሠረቱን ያገኘው ከዚሁ ከ*ኢስቲስሃብ* መርሆ ነው፡፡ ይኸውም ሰው በግል ምርጫውም ሆነ በሕብረተሰባዊ አኗኗሩና ባህሉ ፍትሐዊና የሚጠቅመውን *(ዐድል ወ ኢህሳን)* ይከተላል፤ ይተገብራል ተብሎ ይታሰባል፡፡ የሰው የምክንያታዊነትና የሚዛናዊነት አቅም ከፍተኛ ሸሪዓዊ እውቅናና አጽንኦት የተሰጠው መሆኑን መሠረት በማድረግ ማንኛውም በሸሪዓ ተለይቶ ያልተከለከለ ነገር ሁሉ የተፈቀደ መሆኑ የሰው ተፈጥሯዊ የፍትሕ አስተሳሰብና ያልተዛነፈ የሕሊና ሚዛን ሳይቋረጥ የሚቀጥል መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ በአካባቢያዊ ተጽእኖዎችና በባዕድ አስተሳሰቦች ከመስመር የሚወጣ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ ሸሪዓ ወደ ነበረበት እንዲመለስ በማድረግ ሰብዓዊ-ተፈጥሯዊ ፍትሕና ርትዕ ቀጣይነታቸው እንዲረጋገጥ የሚያደርግ መርሆ ነው፡፡[16]

---

[10] Ahmad Hasan, *The Principle of Istihsan In Islamic Jurisprudence*, 16(4) ISLAMIC STUDIES, 347(1977).

[11] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 347.

[12] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 359.

[13] Felicitas Opwis, *Maṣlaḥa in Contemporary Islamic Legal Theory*, 12(2) ISLAMIC LAW AND SOCIETY, 188 (2005).

[14] አልዩ አባተ ይማም፣ የሸሪዓ እድገትና ቀዳሚ የሕግ ትምህርት ቤቶች፡ ከኢትዮጵያዊ ምልከታዎች ጋር፣ 8 HARAMAYA LAW REVIEW, 77-78 (2019).

[15] KAMALI, SHARIA LAW, ግርጌ ማስታወሻ 8, ገጽ 168.

[16] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 168-169.

ከላይ በአጭሩ የተወሱት የተለያዩ የሕግ ንደፈ-ሐሳቦች በ*መዝሓብ* ሊቃውንት ሲለዩ የራሳቸውን ጽንሰ-ሐሳብና *ሥነ-ሥርዓት* ያዘሉ በመሆናቸው በሸሪዓ ሕግ እድገት ከ*ታቢዑን* ዘመን ጀምሮ ለተስተዋለው *ሥርዓት-የለሽ* ሸሪዓዊ የሕግ ምርምር *(ኢጅቲሓድ)* ወጥ ማዕቀፍ የሚዘረጉ ናቸው። *የኢጅቲሓድ* መርሆዎች ከሚያጋጥሙ አዳዲስ የሕግ ጭብጮች አኳያ እንደአግባብነታቸው *የኢጅቲሓድ* መንደርደሪያ ይሆናሉ። እንዲሁም ዝርዝር የሕግ አመክንዮና የትንታኔ ሂደቱን ይመራሉ፤ ይቆጣጠራሉ። መርሆዎቹ በራሳቸው ከቀዳሚ የሸሪዓ ምንጮች የተቀሰሙ በመሆናቸውና የእነዚህ ምንጮች የሕግ ፍልስፍና ማዕዘናት በመሆናቸው በእነዚህ ቀኖናዎች ላይ በመመርኮዝ ለአዳዲስ የሕግ ጭብጦች መፍትሔ በመሆን የሚቀረጹ ዝርዝር የሕግ ድንጋጌዎች *(አህካም)* ከጠቅላላ የሸሪዓ ዓላማዎች *ጋር* እንዲጣጣሙ እና እንዲያሳኩ ያደርጋሉ።[17]

አጠቃላይ የ*ኢጅቲሓድ ሥነ-ሥርዓቱ*ን ለማሳየት ያህል ከላይ በተዘዋዋሪ መልኩ እንደተወሳው በየትኛውም ጊዜ እና ሁኔታ ላይ እንደ ጭብጥ *(ፈርዕ)* ሆኖ የሚነሳ የሕግ ጥያቄ ሁሉ ግልጽና ልዩ ድንጋጌ *(ነስ)* አርፎበት ከሆነ በመጀመሪያ ከቁርአን እና ከ*ሱናሕ* ሊፈተሽ ይገባል። ይህ በሌለበት ጉዳዩን በተዘዋዋሪ የሚዳስስ ወይም አጠቃላይ ፍንጭ የሚሰጥ ድንጋጌ ቢኖር የሸሪዓ የአተረጓጎም ደንቦችን ተፈጻሚ በማድረግ ለአዲሱ ጭብጥ ተስማሚ ድንጋጌ ይቀረጻል። ጭብጡን በየትኛውም አኳኋን የሚመለከት ልዩ ድንጋጌ በቁርአን ወይም በ*ሱናሕ* የሌለ እንደሆነ ከዓላማ *(ዒላሕ)* አኳያ ከተያዘው ጭብጥ *ጋር* የሚመሳሰል ነባር ድንጋጌ ያለ እንደሆነ በ*ቂያስ* አማካይነት ነባሩ ድንጋጌ በአዲሱ ጉዳይ ላይ ተፈጻሚ ይደረጋል። ተያያዥ የሸሪዓ ምንጮችን አቀናጅቶ በመተንተን ሂደት ላይ ግጭት ቢያጋጥም በ*ኡሱል* ሊቃውንት የዳበረውን የሸሪዓ አተረጓጎም ዘዴዎች በተለይ የግጭት አፈታትና የአስረጅ ምርጫ *(ተዓሩድ ወ ተርጂሕ)* ደንቦችን ተፈጻሚ በማድረግ ማስታረቅ ወይም ጠንካራና አሳማኝ የሆነው አስረጅ ሊመረጥ ይገባል።[18]

ለተነሳዉ ጭብጥ ከላይ በተቀመጠው መሠረት የሕግ መፍትሔ ሊበጅለት ካልቻለ *ኢጅቲሓድ* ከትርጉም ሚናዉ በዘለለ እንደ *ኢስቲስላሕ* (የሕዝብ ጥቅም) *ኢስተቲህሳን* (ርትዕ) *ሰድ አዝ-ዘራኢዕ* (ከምንጩ ማድረቅ) ከመሳሰሉ ፓሊዮቶች መካከል ለጭብጡ የሕግ እልባት ለመስጠት ይበልጥ ተስማሚ የሆነው ተመርጦ ለሕግ አወጣጥ መነሻ ይደረጋል።[19] ባጠቃላይ ግልጽ የ*ኑሱስ* መፍትሔ በሌለበት *ፈርዕ* ላይ *የኢጅቲሓድ ሥርዓ*ቱ የሚኖረው ከጭብጡ *ጋር* ተዛማጅነት ያላቸውን አስረጂዎች በመተንተን ከምንጮች ላይ ድንጋጌዎችን መቅሰም *(ኢስቲንባጥ/Deduction)* ሲሆን ይህ አይነቱ የሕግ ምርምር አብራሪ/ተንታኝ *ኢጅቲሓድ (ኢጅቲሓድ በያኒ)* ይባላል። በቁርአን ወይም በ*ሱናሕ* ውስጥ ስለጭብጡ ምንም ፍንጭ የሌለ ከሆነ ደግሞ ከአዲሱ ጭብጥ *ጋር* የዓላማ ተመሳሳይነት ያለው ነባር ድንጋጌ ተለይቶ የአጠቃላይ የሸሪዓ ዓላማዎችን በማይቃረን አኳኋን ተፈጻሚ ይደረጋል፤ ይህ አይነቱ *ኢጅቲሓድ* ምስስሏዊ *ኢጀቲሓድ (ኢጀቲሓድ ቂያሲ)* ይባላል።[20]

ምንም እንኳን *ኢጅቲሓድ* እንደ ሻፊዒ አተያይ በ*ቂያስ* ላይ የተወሰነ ቢሆንም ብዙኃኑ *ዑለማእ* ግን *ቂያስ* ማድረግ የማይቻልበት ጉዳይ ካጋጠመ ሌሎች እንደ *ኢስቲስላሕ* ያሉ መርሆዎች መንደርደሪያ ሊደረጉ *(ኢጅቲሓድ ኢስቲስላሂ)* እና የሸሪዓ ድንጋጌዎችና ፍርዶች ሊሰጡ እንደሚገባ ይስማማሉ።[21] *ኢጅቲሓድ* በማድረግ ሒደት ውስጥ በተያዘው ጭብጥ ላይ ሌሎች *መዝሓቦችና* የሸሪዓ ሊቃውንት *(ሙጀተሒዱን)* የደረሱበት የ*ጋራ* ወይም የግል የሕግ ድምዳሜ ካለ የምርምሩ አካል ሊደረግ የሚገባ መሆኑን ለተመራማሪው ወሰኝና አቋምን እስከማስቀየር የሚደርሱ ምልከታዎች የሚገኙበት የካበተ የእውቀት አሻራ ያለ መሆኑ አያጠራጥርም።[22] ከዚህ ሁሉ በኋላ ለጉዳዩ መፍትሔ የሚሆን መነሻ ሐሳብ በሌለበት ጊዜ፣ ሰው በተፈጥሮው ነጻ ሆኖ የተፈጠረ ከመሆኑና አሳሪ ሕግ ወይም የውል ስምምነት በሌለበት ሰብዓዊ ነጻ ምርጫ *(አል-በራኣሕ አል-አስሊያሕ)* የተረጋገጠ መሆኑን መሠረት በማድረግ ለግለሰቡ *(ሙከለፍ)* ምርጫ ሊተው የሚችልበት የመጨረሻ አማራጭ ይገኛል። በመጨረሻም በጭብጡ ላይ

---

[17] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 169.

[18] MOHAMMAD HASHIM KAMALI, PRINCIPLES OF ISLAMIC JURISPRUDENCE, 379-380 (Cambridge፡The Islamic Texts Society, 1991).

[19] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 379.

[20] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 380.

[21] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 379-380.

[22] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 380.

የሚደረገው *ኢጅቲሓዳዊ* ምርምር የ*ዋጂብ* (አስገዳጅ) *ሀራም* (ክልክል) *መክሩሕ* (የተጠላ) *መንዱብ* (የተወደደ) ወይም ፍቁድነት *(ኢባሃሕ)* የድንጋጌ ቅርጽ ይዞ ይደመደማል፡፡[23]

በምርምር ሂደትም ላይ በተለይም የአተረጓጎም ደንቦችን ተፈጻሚ በማድረግና በጥቅል መርሆዎች ላይ በመመርኮዝ ልዩ ድንጋጌ ላይ በመድረስ ሂደት ላይ፣ ከቃል በቃል የሕግ አረዳድ ይልቅ ጠቅላላ የሸሪዓ ዓላማዎችና ግቦች *(መቃሲድ አሽ-ሸሪዓሕ)* እውን የሚሆኑበትን አተረጓጎም መከተል አስፈላጊ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡[24] በተጨማሪም የሸሪዓ ምንጮችን እርስ በርስ አስተሳስሮ በመተንተን ሒደት ውስጥ ተቃርኖዎች ቢያጋጥሙ የአስረጂዎችን ግጭት ለመፍታት የዳበሩ የአተረጓጎም ደንቦች *(አት-ተዓሩድ በይን አል-አዲላሕ)* ተፈጻሚ ሊደረጉ ይገባል፡፡[25]

*በታቢዑን* ዘመን የተነሱ የ*መዝሓብ* መስራቾች እና ተማሪዎቻቸው *(ኡሱሊዩን)* ያረቀቋቸው የሕግ መርሆዎችን በአንድነት በማጥናት እርስ በርስ ያላቸውን ትስስርና የአስረጂነት ደረጃ በመመዘን አጠቃላይ *የኢጅቲሓድ ሥርዓቱን* ከላይ በአጭሩ በተመለከተው አኳኋን የቀረጹት ታላቁ የሕግ ሊቅ ኢማም አሽ-ሻፊዒ መሆናቸው ሳይጠቀስ አይታለፍም፤ ከዚህ ሚናቸው አንጻር የሸሪዓ መሠረተ-ሐሳቦች *(ኡሱል)* መስራች እየተባሉ ይጠራሉ፡፡[26]

## ሐ. የሙሀመድ እና የባልደረቦቻቸው ኢጅቲሓድ

እዚህ ላይ የሚነሳው መሠረታዊ ጥያቄ ነቢዩ ሙሀመድ የሚሰጧቸው ብይኖች በሙሉ በመለኮታዊ ራዕይ የተገለጹ ናቸው ወይስ እንደ አንድ ግለሰብ *ሙጅተሒድ* ወይም አመራር ግላዊ *ኢጅቲሓድ* ያደርጉ ነበር የሚለው ነው፡፡ ሙሀመድ በእምነት ወይም በሥነ-መለኮታዊ ጉዳዮች ላይ ሳይሆን በወቅታዊና ወታደራዊ ጉዳዮች ላይ የራሳቸውን የግል ሚዛንና አተያይ መሠረት በማድረግ የራዕይ *(ወህይ)* አጀብ የሌለው ውሳኔና አመራር ያሳልፉ እንደነበር በብዙኃኑ *ዑለማእ* ዘንድ የታመነ ነው፡፡[27] አሽዓሪዎች ሙዕተዚላዎች ዟሒሪዎች እና የሻፊዒ እና የሃንበሊ ሊቃውንት ደግሞ በ*ሱራሕ* አን-ነጅም (53፡3) ‹መለኮታዊ ራዕይ ተገለጾለት ቢሆን እንጂ ከራሱ ፍላጎትና ልብ-ወለድ አይናገርም› የሚለውን አስረጅ ተመርኩዘው ሙሀመድ ከነቢይነት ደረጃቸው ውጪ በግል አስተያየታቸው *(ኢጅቲሓድ)* የተናገሩት ወይም የተገበሩት ነገር የለም የሚል አቋም አላቸው፡፡[28]

---

[23] ዝኒ ከማሁ.

[24] አልዩ አባተ ይማም፣ የሸሪዓ ሕግ ዓላማዎች (መቃሲድ አሽ-ሸሪዓሕ)፣ 7(2) የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሕግ መጽሔት፣ 274-275 (June 2017)::

[25] KAMALI, PRINCIPLES, *ግርጌ ማስታወሻ* 18, ገጽ 380.

[26] Mohd Daud Bakar, *The Origins of Islamic Jurisprudence (Usul al-Fiqh)*, 5(2) Intellectual Discourse, 123(1997).

[27] Mohamed Abdel-Khalek Omar, *Reasoning in Islamic Law: Part Two*, 12(4) ARAB LAW QUARTERLY, 371(1997). ከዚህ ነቢያዊ የኢጅቲሓድ ጽንሰ-ሐሳብ ወጥ አተያይ ጋር በተያያዘ፣ ከነቢዩ የተዘገቡ የሀዲስ ዘገባዎች በሦስት ምድቦች ተከፍለው ይታያሉ፡ መለኮታዊ ምንጭ እና ምሪት ያላቸው ነቢያዊ ንግግሮች እና ተግባራት፡፡ እነዚህ ዘገባዎች ሙሀመድ በነቢይነት ደረጃቸው ያስተላለፏቸው መልዕክቶች እና አረዓያ የሆኑባቸው የአስተሳሰብ እና የምግባር ተምሳሌቶችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ይህን የ*ሱናሕ* ክፍል፣ እንደ አስገዳጅነት ደረጃቸው መከተል እና መተግበር ከሁሉም አማኝ የሚጠበቅ ነው፡፡ ሙሀመድ በፖለቲካ አመራርነታቸው በተለያየ ማህረሰባዊ እና ወታደራዊ ጉዳዮች ላይ የሰጧቸው ወቅታዊ እና አውዳዊ ውሳኔዎች ሁለተኛውን የ*ሱናሕ* ክፍል ይይዛሉ፡፡ እነዚህ ውሳኔዎች መከተል እና መፈጸም የሁኔታዎች መመሳሰልና እና ውሳኔው የተሰጠበትን አውድ የተከተለ እስከሆነ ድረስ መከተሉ ተመራጭ ቢሆንም ሙሀመድ በነቢይነት ሳይሆን በአመራርነታቸው፣ የግል *ኢጅቲሓድ* በማድረግ የደረሱባቸው ድምዳሜዎች እና አካባቢያዊ ምዘናዎች በመሆናቸው በየትኛውም ቅርጽ ቢሆን አስገዳጅነት የሌላቸው መሆኑን፣ በአማራጮነት ታሳቢ ሊደረጉ የሚገቡ የ*ኢጅቲሓድ* አስተያየቶች በመሆናቸው፣ ከነቢያዊ ዘገባዎች ጋር ተቀላቅለው በ*ሀዲሶች* ይተላለፉ እንጂ እንደመጀመሪያው አይነት *ሱናዎች* አስገዳጅነት የሌላቸው መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ሙሀመድ እንደ ማንኛውም ግለሰብ ሁሉ የራሳቸው የግል ሕይወት ዝንባሌ እና ምርጫ ያላቸው በመሆኑ በግል ሕይወታቸው ያከናወኗቸው ተግባራት በሙሉ ነቢያዊ ወይም *ኢጅቲሓዳዊ* ፋይዳ የሌለው መሆኑን ይገነዘቧል፡፡ ግልጽ ትዕዛዝ ወይም ክልከላ ያልተሰጠባቸው እንዲሁ አመጋገባቸውን የቀለም ምርጫቸውን አለባበሳቻውን ወዘተ.. የሚዘግቡ *ሀዲሶች* በሙሉ የ*ሱናሕ* ወይም ሃይማኖታዊ ፋይዳ የሌላቸው መሆኑን መረዳት ያሰፈልጋል፡፡ (አልዩ አባተ፣ *ሱናሕ፦ ሁለተኛው የሸሪዓ ሕግ ምንጭ*፣ 3 HAWASSA UNIVERSITY JOURNAL OF LAW, 157-160 (July, 2019)).

[28] KAMALI, PRINCIPLES, *ግርጌ ማስታወሻ* 18, ገጽ 381. በእነዚህ ምሁራን አተያይ ደግሞ የ*ሀዲስ* ዘገባዎችን በሦስት መመደብና የተለያየ የአስረጂነት ፋይዳ መስጠት ተቀባይነት የለውም፡፡ ማንኛውም ተዓማኒ የሆነ ዘገባ የትኛውም የሙሀመድ እንቅስቃሴ ሙሉ ነቢያዊ እና መለኮታዊ አመራርነት የተላበሰ ነው የሚል አቋም አላቸው፡፡

እንደ ብዙኃኑ *ዑለማኦ* አተያይ ደግሞ ሙሀመድ ባልደረቦቻቸውና ጠቅላላው አማኝ ማህበረሰብ በቁርአን አንቀጾች ላይ እንዲሁም በዙሪያው ባለው ፍጥረተ-ዓለም ላይ እንዲያስብና እንዲመራመር ቁርአናዊ ጉትጎታ መደረጉ ሙሀመድና ባልደረቦቻቸው በሚያጋጥማቸው ዓለማዊ ጉዳዮች ላይ ሁልጊዜም መለኮታዊ ራዕይ መጠበቅ እንደሌለባቸው እና የራሳቸውን አካሄድ መከተል እንደሚገባቸው ያስገነዝባል። በአስረጂነት የቀረበውን የምዕራፍ አን-ነጅምን አንቀጽ በተመለከተ አንቀጹ የቁርአንን ፍጹም መለኮታዊነት የሚገልጽ መሆኑን በተለይ ‹ይህ *(ሑወ)*› የሚለው ተውላጠ ስም ቁርአንን የሚወክል በመሆኑ ሙሀመድ ቁርአን ብሎ የራሱን እሳቤ እንደማይናገር የሚያረጋግጥ ነው። በተጨማሪም አንቀጹ የወረደበትን ከባቢያዊ ሁኔታ *(ሸእን አን-ኑዙል)* ስንመለከት የመካሕ ከሃዲያን ቁርአን የራሱ የሙሀመድ ፈጠራ ነው አምላክ ያወረደው አይደልም እያሉ በሚያስተባብሉበት ወቅት ምላሽ በመሆን የወረደ አንቀጽ መሆኑ አንቀጹ ስለቁርአን መለኮታዊ ቃልነት የሚገልጽ እንጂ ሁሉም የሙሀመድ ንግግሮችና ተግባራት በ*ወሀይ* የተመሩ ናቸው ለማለት እንዳልሆነ አብዛሀኞቹ ምሁራን ያስረዳሉ።[29] በተያዘው ጭብጥ ላይ ከሚቀርቡ ሐሳባዊ መከራከሪያዎች ሌላ፣ ሙሀመድ በመሪነታቸው በተግባር ይገጥሟቸው የነበሩ ችግሮችን ለመፍታት ከግል ውሳኔያቸውና ከባልደረቦቻቸው *ጋር* ባደረጓቸው ምክክሮች ውስጥ ምስስሎአዊ አመክንዮንና *ኢጅቲሓድን* በተጨባጭ የተገበሩ መሆኑን በግልጽ የሚያመላክቱ በርካታ *አጋ*ጣሚዎችን ይጠቅሳሉ። ለምሳሌ ከበድር ጦርነት በኋላ በሙስሊሞች እጅ የወደቁ ምርኮኞችን በተመለከተ ሙሀመድ ከጓደኞቻቸው *ጋር* ምክክር አድርገው የአቡ-በክርን ሐሳብ ተቀብለው ተፈጻሚ ማድረጋቸው ከነቢይነት ሚናቸው በተጨማሪ እንደ አመራር *ኢጅቲሓድ* የሚያደርጉ ለመሆኑ አንድ አብነት ነው። በዚህ ሁኔታ ላይ የተወሰደው እርምጃ የተሳሳተ መሆኑን የሚገልጽ ቁርኣናዊ አንቀጽ መውረዱ ደግሞ ውሳኔው ከመነሻውም ከ*ኢጅቲሓድ* የመነጨ መሆኑን ያረጋግጣል። በሌላ በኩል ከተቡክ ዘመቻ በኋላ በዘመቻው ያልተካፈሉ የመዲና ነዋሪዎች ያልተሳተፉበትን ምክንያት ወደ ነቢዩ ዘንድ እየመጡ ሲገልጹ ነቢዩም ምክንያታቸውን መቀበላቸውና ይቅር ማለታቸው በግል ግምገማቸው የያዙት *ኢጅቲሓዳዊ* አቋም መሆኑን በሚያስረዳ ሁኔታ ነቢዩ የተከተሉት *ፖ*ሊሲ ስህተት መሆኑን የሚያስገነዝቡ የቁርአን አንቀጾች ወርደዋል።[30] ሙሀመድ ከነቢይነት ሚናቸው በተጨማሪ *ኢጅቲሓድ* ያደርጉ የነበረ መሆኑን *ሀዲሳዊ* ማስረጃዎችም ሊጠቀሱ ይችላሉ፤ ከእነዚህም መካከል በግንባር ቀደምነት የሚጠቀሰው‹እኔ (ሙሀመድ) ራዕይ ያልተገለጸልኝ ከሆነ የግል እይታዬን *(ረእይ)* መሠረት በማድረግ እፈርዳለሁ› እንዳሉ የሚዘግበው *ሀዲስ* ነው።[31]

በተመሳሰይ መልኩ ባልደረቦችም ቢሆኑ ሙሀመድ በሕይወት በነበሩባቸው ጊዚያት በተለይ ደግሞ ከቦታ ርቀት አኳያም ሆነ በሌሎች ምክንያቶች ሁሉንም ጉዳዮች ለነቢዩ ማቅረብ በማይቻልባቸው *አጋ*ጣሚዎች ላይ ሁሉ ከሙሀመድ ራዕያዊ ወይም *ኢጅቲሓዳዊ* አመራር ሳይጠብቁ የራሳቸውን የግል *ኢጅቲሓድ* በማድረግ ዳኝነት የሰጡ መሆኑን የሚያስረዱ ብዙ የ*ሀዲስ* ዘገባዎች ይገኛሉ። ለምሳሌ ሙዐዝ ኢብን ጀበል ለየመን ክፍለ-ግዛት በዳኝነት ተሹሞ መላኩን የሚዘግበው *ሀዲስ* ሙስሊሞች ከጠላት *ጋር* በተፋጠጡበት ወቅት አጎራባች የበኑ ቁረይዟ አይሁዶች በሰላም አብሮ የመኖር ቃል-ኪዳናቸውን አፍርሰው ሙስሊም ሲቪል ነዋሪዎች ላይ ወታደራዊ ጥቃት መፈጸማቸውን ተከትሎ ነቢዩ ባሉበት በጉዳዩ ላይ ባልደረባቸው ሰዕድ ኢብን ሙዓዝ በሰጠው ውሳኔ መሠረት ወታደራዊ እርምጃ መውሰዳቸውን የሚዘግቡት *ሀዲሶች* ተጠቃሽ ናቸው።[32]

## መ. የኢጅቲሓድ/ሙጅቲሒድ እርከኖች

በ5ኛው *ም.ሒ*/11ኛው ም.ል ገደማ[33] በቀደመው የሸሪዓ እድገት *ታሪክ* ያልታየ የ*ኢጅቲሓድ* ወይም የ*ሙጅተሒድ* ደረጃዎችና እርከኖች መውጣት ጀመሩ። ለመጀመሪያ ጊዜ *ኢጅቲሓድን* በሁለት ደረጃዎች የከፈሉት ሊቅ ኢማም አል-ገዛሊ ናቸው። ከዚያም በተከታዮች ዘመናት የተነሱ ምሁራን እርከኖቹን ወደ አምስት ከዚያም ወደ ሰባት አድርሰዋቸዋል። ከጊዜ በኋላ የ*ኢጅቲሓድ* እርከኖችን የማውጣት እድገቶች የመጡበት የጀርባ ምክንያት ሲታይ እንደ ቀደምት የ*መዝሓብ* መስራቾች ብቁ የሆነ፣ በቀጥታ ከሸሪዓ ምንጮች ላይ በመመርኮዝ የ*ኢጅቲሓድ* መርሆዎችን ወይም አዲስ የሕግ ድምዳሜዎች ላይ መድረስ የሚችል ተመራማሪ *(ሙጅተሒድ)* የለም፤ ወይም ‹የ*ኢጅቲሓድ* በር

---

[29] *ዝኒ ከማሁ.*

[30] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 382; እንዲሁም ቁርአን፣ 9፡43-49 ይመለከቷል።

[31] ዝኒ ከማሁ.

[32] Omar, *Reasoning in Islamic Law*, ግርጌ ማስታወሻ 26, ገጽ 371.

[33] ም.ሒ (ምዕተ-ሒጅራ)፣ ም.ል (ምዕተ-ልደት).

ተዘግቷል› ከሚል በወቅቱ የነገሰ እሳቤ የመነጨ ነው። ይህ እሳቤ በዘመኑ የሸሪዓ ሊቃውንት ከፍተኛ ነቀፌታ የቀረበበትና ለዓለም ሙስሊም ማህበረሰብ የእምነትና የሥልጣኔ መንጠፍ ዋነኛ መንስኤ እንደሆነ በጭፍን ተከታይነት ያልታሰረ ነጻ አመክንዮኣዊ ምርምር እንደገና ሊያንሰራራ እንደሚገባና የቀዳሚው የባልደረቦችና የተከታዮች ትውልድ አካሄድ መከተል እንደሚገባ ያሳስባሉ።[34] በዚህ ክፍል የ*ኢጅቲሓድ* እርከኖች ሲዳሰሱ *የኢጅቲሓድ* በር ተዘግቷል በሚል እሳቤ ወይም በዚህ ዘመን መስራች *ሙጅተሒድ* መሆን የሚችል የለም፤ ወይም ከዚያ በታች ባሉት እርከኖች ስር ከተደለደሉ ሊቃውንት ውጭ ሌሎች ሊቃውንት *የሙጅቲሒድነት* ሚና ሊኖራቸው አይችልም በሚል እሳቤ አይደለም፤ ይልቁንም እንደ እውነታ አንድ የሸሪዓ ሊቅ በሚያደርገው ምርምር ከሌሎች *የመዝሓብና* የግል ሊቃውንት አኳያ ሊኖረው የሚችለውን ሚና ለማመላከት ያህል መሆኑን ይገነዘቧል። በመሆኑም ከሁለት ጀምሮ እስከ ሰባት *የሙጅተሒድነት* ሚናዎች በመስኩ ሊቃውንት የተዘረዘሩ ቢሆንም ተቀራራቢነት ያላቸውን በአንድነት ተጠቃለው እንደሚከተለው በሦስት የ*ኢጅቲሓድ* ደረጃዎች ስር ተዳሰዋል።[35]

## 1. መስራች ሙጅተሒድ (ኢጅቲሓድ ፊ ሸርዕ)

በቁርአንና በ*ሱናሕ* ላይ በመመራመር የመጀመሪያ የሆነ የሕግ ድምዳሜ ላይ መድረስ ቀዳሚ/ኦርጂናል *ኢጅቲሓድ (ኢጅቲሓድ ፊ ሸርዕ)* ይባላል። ከሙህመድ ባልደረቦች መካከል የጥልቅ እሳቤ ባለቤት የነበሩት ሊቆች እንዲሁም እነሱን ተከትለው የመጡት የተከታዮች *(ታቢዑን)* ዘመናት ሊቃውንት ነጻ አመክንዮን በመጠቀም፣ ከእነሱ በኋላ ከተቋቋሙት የ*መዝሓብ* ማዕቀፍና መርሆዎች ስር ሳይሆኑ በግል የየራሳቸውን ምርምር በማድረግ የሕግ መርሆዎችና ድንጋጌዎች ላይ ይደርሱ ስለነበር በዚህ ምድብ ስር የሚመደቡ ናቸው። ለምሳሌ የአቡ-ሀኒፋ መምህር የሆኑት ኢብራሒም አንነኢ ሰዕድ ኢብን አል-ሙሰይብ የአራቱ *መዝሓብ* መስራቾች የሺዓ *ኢማሚያ ሥ*ርዓት መሪዎች የሆኑት ሙሀመድ አል-ባቂርና ልጃቸው ጀዕፈር አስ-ሷዲቅ አል-አውዛዒና ሌሎች መሰል ሊቃውንት መስራች *ሙጅተሒዶች* መሆናቸው ይታወቃል። እነዚህ *ሙጅተሒዶች* ዝርዝር የ*ፊቅሕ* ድንጋጌዎችን ለመቅረጽ ወይም ብይኖችን ለመስጠት እንደ *መስላሃሕ ኢስቲህሳን ቂያስ ኢጅማዕ* የመሳሰሉ የሕግ መሠረተ-ሐሳቦችን በመለየት ለተከታዩ ትውልድ እና ምሁራን የእውቀት መሠረት ዘርግተው አልፈዋል።[36]

ከመዝሓቦች መመስረት በኋላ በ5<sup>ኛው</sup> መቶ ዓ.ሒ *ሙጀቲሒድ* ለመባል የተቀመጡት መስፈርቶች *(ሹሩጥ)* በጣም ውስብስብና ከባድ ናቸው፤ ስለሆነም ኦርጂናል ሸሪዓዊ ምርምር ማድረግ የሚችል የለም የ*ኢጅቲሓድ* በር ተዘግቷል የሚል አቋም በሀነፊ ማሊኪ እና ሻፊዒ *ዑለማጰ* በኩል ተንጸባርቋል። ከመስራች ኢማሞች በኋላ *ለሙጅቲሒድነት* ደረጃ ደርሰዋል ተብለው በሚጠቀሱ ሊቃውንት ላይ የተለያዩ *የሙጅተሒድነት* ምዘና አቋሞች ከግራና ቀኝ ተሰንዝረዋል። ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ የሀንበሊ ምሁራን እና የሺዓ *ኢማሚያ* ሊቃውንት *ኢጅቲሓድ* በር ተዘግቷል የሚለውን ሐሳብ ነቅፈው ተከራክረዋል ከዚህ የተለየ አቋም ይዘዋል።[37] እነዚህና የክፍለ-ዘመኑ የኢስላም ሊቃውንት ደግሞ *ሙጀተሒድነት* ካለው ጥብቅ ቅድመ-ሁኔታዎች በመነሳት ካላፉት የ*ሑሱል* ምሁራን ሕልፈት በኋላ *ሙጅቲሒድ* መሆን የሚችል የለም የሚለው ሐሳብ አንድምታ አንድም የሸሪዓ ሕግ ለብዘኃኑ ትውልድ አግባብነት የሌለውና ጊዜው ያለፈበት ነው ማለት ነው። ወይም ደግሞ ከሺህ ዓመታት በፊት የተቀረጹ የሸሪዓ መርሆዎችና ሕጎች ምንም ማሻሻያ ወይም ጭማሬ ሳይደረግባቸው ለዘመኑ የሙስሊም ሕብረተሰብ እንደነበሩ ተፈጻሚ ይደረጋሉ ማለት ነው። በሁለቱም በኩል ቢሆን ምክንያታዊነት የጎደለው ነው። ሸሪዓ እስካለ ድረስ *ኢጅቲሓድ* በር ሊዘጋ አይችልም። ምክንያቱም የሸሪዓ ሕግ በዘመን ሳይገደብ ያለውን እና የወደፊቱን የሙስሊም ትውልድ ዘርፈ-ብዙ ግንኙነትን በሕግ ለመግዛት ይቻል ዘንድ *ኢጅቲሓድ* ቁልፍ መሳሪያ ነው።

*ሙጅተሒድ* መሆን የሚችል የለም የሚለው የተዛባ እይታ የመነጨው *የኢጅቲሓድ* መስፈርቶቹን የሚያሟላ ሳይኖር ቀርቶ ሳይሆን ቀደም ባለው ክፍል አንደተብራራው ከ*ኢጅቲሓድ* ተከፋፋይነት ባህሪ አኳያ የተቀመጡት

---

[34] KAMALI, PRINCIPLES, ግርጌ ማስታወሻ 18, ገጽ 386.

[35] በሰባቱ የሙጅተሒድ እርከኖች ላይ ተናጠላዊ ማብራሪያ ለማግኘት የከማሊን Principles, ግርጌ ማስታወሻ 18, ገጽ. 386-389 ይመለከቷል።

[36] KAMALI PRINCIPLES, ግርጌ ማስታወሻ 18, ገጽ 386.

[37] M. Ṣaghīr Ḥasan Ma'ṣūmi, *Ijtihād through Fourteen Centuries*, 21(4) ISLAMIC STUDIES, 62 (Winter 1982).

መስፈርቶች የተጋነኑና አላስፈላጊ ቅድመ-ሁኔታዎችን ያካተቱ በመሆኑ[38] የችግሩ ዋነኛ መንስኤ በቀድሞ የ*ኡሱል*ና የ*ፊቅሕ* ምሁራን ላይ ጥገኛ የመሆንና የጭፍን ተከታይነት አስተሳሰብ *(ተቅሊድ)* እንደሆነ ያስገነዝባሉ።[39] ከሕግ መርሆዎችና ዝርዝር ድንጋጌዎች ባሻገር *ኢጅቲሓድ* በራሱ ምንድን ነው *ሙጀተሒዶች* እነማን ናቸው የሚሉት ጥያቄዎች በራሳቸው የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ መሠረት ያደረገ ትርጓሜና መስፈርት ሊቀመጥላቸው የሚገባ እንጂ በጥንታዊ ትርጓሜያቸው እንደጸኑ የሚቀጥሉበት ምንም ምክንያት የለም።

በተጨማሪም *ኢጅቲሓድ* ማድረግ የግል ወይም የማህበረሰቡ ግዴታ *(ፈርድ ዐይኒ እና ከፋኢ)* መሆኑ የማይታበል እስከሆነ ድረስ ይህ ግዴታ ሊፈጸም የሚችለው ደግሞ ኦርጂናል *ኢጅቲሓድ* ተቋርጧል ሲባል ሳይሆን በየዘመናቱ የሚነሱ ሊቃውንት ሸሪዓን ከወቅቱ የማህበረሰብ ሥልጣኔና እውነታዎች ጋር አጣጥመው *ኢጅቲሓድ* ማድረግ ሲቻል በመሆኑ የ*ኢጅቲሓድ* በር ሁልጊዜም ክፍት ነው በማለት ተከራክረዋል።[40] ሀንበሊዎች ከ*ኢጅቲሓድ* የቀጣይነት ባህሪ በተጨማሪ የትኛውም ዘመን *(ዐስር)* ወይም ትውልድ *ሙጅተሒድ* ሳይነሳበት አይቀርም የሚል እይታ ያከሉ ሲሆን ሺዓዎች ደግሞ የ*ኢማሚያ ሥርዓታቸውን* መሠረት በማድረግ *ኢጅቲሓድ* በዋናነት በተመረጡ መሪዎቻቸው *(ኢማሞች)* አማካይት የተከናወነ ሲሆን በእነሱ ምርምር ያልተሸፈኑ ጭብጦች በተነሱ ጊዜ ኢማሞቻቸው ካወጧቸው መርሆዎችና ድንጋጌዎች ጋር በማይቃረን አኳኋን *ኢጅቲሓድ* ሊደረግ እንደሚችል እና በጥቅሉ አመክንዮ ከቁርአንና

---

[38] KAMALI, PRINCIPLES, *ግርጌ ማስታወሻ* 18, ገጽ 377. አንድ የሸሪዓ ሊቅ *ኢጅቲሓድ* ለማድረግ በቅድሚያ ሊሟሉ ይገባል ተብለው በመስኩ *ሥነ-ጽሁፍ* የተለዩ መመዘኛዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የቁርኣን ጥናቶች (ዑሉም አል-ቁርኣን)፡- የመኪይ እና መደኒ የቁርአን ምዕራፎችና አንቀጾች እውቀት፣ የቁርአን አረብኛ (Quranic Arabic) እውቀት በተለይ የቁርአን የሕግ ክፍል (ፊቅሕ አል-ቁርአን) የሸሪዓ የሕግ መሠረት በመሆኑ ለኢጅቲሓድ እጅግ ወሳኙ የቁርአን ሳይንሶች ክፍል ነው።
2. የሀዲስ ተዓማኒነት ምዘና ጥናት (ኡሱል አል-ሀዲስ)፡- የሕግ ይዘትና አንደምታ ያላቸው ሕግ-ነክ የሀዲስ ዘገባዎች (አሃዲስ አል-አህካም) እንደ ቁርኣናዊ ሕግ-ነክ አንቀጾች ሁሉ ለኢጅቲሓድ ተግባር ቀጥተኛ ግብዓት በመሆናቸው ሙጅተሒዱ በዚህ የሀዲስ ጥናት ክፍል ላይ ሰፊና ጥልቅ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል። የሀዲስ ዘገባዎች የተዓማኒነት ጥያቄ ሊነሳባቸውና አንዳንዴም ሐሳብ ተቃርኖዎችን ሊያስተናግዱ ስለሚችሉ የተዓማኒነት መመዘኛዎች ዘዴዎችን በኡሱል አል-ሀዲስ (የሀዲስ ምዘና መሠረቶች ጥናት) ዘርፍ ስር በቂ ግንዛቤ ሊጨብጥ ይገባል።
3. የሸሪዓ ሕግጋት ጥናት (ፊቅሕ/ፉሩዕ)፡- በቁርአን ሱናሕና በቀደመው የመዛሒብና የሊቃውንት ኢጅቲሓድ የዳበረውን ሙጀተሒዱ ኢጅቲሓድ በሚያደርግበት ዘርፍ ላይ ያለውን ነባር ሸሪዓ ሕግ ማዕቀፍ ማወቅ፣ ለኢጅቲሓድ እጅግ ጠቃሚ ግብዓት ነው። ተመራማሪው ኢጅቲሓድ በሚያደርግበት ጉዳይ በቂ ሳይንሳዊ እውቀት ሊኖረው ይገባል። ይህ ባልሆነበት ሙጅተሒዱ ከሸሪዓ እውቀት ውጪ ሕግ በሚወጣበት የግንኙነት ዘርፍ ላይ ሳይንሳዊ እውቀት የሌለው ከሆነ የመስኩን ልሒቃን ምሁራዊ እገዛ ማግኘት የግድ ይሆናል። ስለዚህ በአንድ ዘርፍ ላይ ተገቢውን የሕግ ማዕቀፍ ለመዘርጋት ከነባሩ የፊቅሕ እውቀት በተጨማሪ የዘመኑን ማህበረሰብ ተጨባጭ ላይ ያለውን ሳይንሳዊ እውቀት የተንተሰራሰ ሕጎችን ለማስተዋወቅ አግባብነት ያለውን የሳይንስ መስክ በቅጡ ማወቅ አሊያም ከመስኩ ምሁራን አስፈለጊውን እገዛ ማግኘት (የሕብረት ኢጅቲሓድ - ኢጅቲሓድ ጀማዒ) የግድ ይላል።
4. የሸሪዓ መሠረተ-ሐሳቦች ጥናት (ኡሱል አል-ፊቅሕ)፡- ይህ የጥናት መስክ ማንኛውም ልሂቅ ሸሪዓዊ የሕግ ምርምር ለማድረግ ይችል ዘንድ ሙሉ በሙሉ ሊካንበት የሚገባ የእውቀት መስክ ነው። ምክንያቱም የአሱል ትምህርት ዋነኛ ዓላማ ሸሪዓዊ የሕግ ምርምርን መምራትና መቆጣጠር በመሆኑ ያለ ኡሱል እውቀት ኢጅቲሓድ ማድረግ የማይታሰብና ለከባድ ሕጸጽ የሚዳርግ ነው። የኡሱል ትምህርት ለሕግ ምርምር መንደርደሪያ የሆኑ ቁርኣናዊ ወይም ሱናዊ የሕግ መርሆዎችን የሚያቀርብና የሚተነትን የቁርአንና የሱናሕ የሕግ ድንጋጌዎችን የአተረጓጎም ደንቦችን የሚዘረጋ ሲሆን እግረ-መንገዱን ከቋንቋም ሆነ ከሕግ ሙያዊ የአተረጓጎም መርሆዎች አማካይነት ኢጀቲሓዳዊ የሕግ ትንታኔ ከግል ስሜት ዘፈቀደኝነትና ወገንተኝነት እሳቤ በራቀ አኳኋን ገለልተኛና ምክንያታዊ በሆነ አቀራረብ እንዲፈጸም ያረጋግጣል። የኡሱል እውቀት አካል በመሆን ከጥቂት ዓመታት ወዲህ የክፍለ-ዘመኑን መምህራን ትኩረት እያገኘ የመጣው ርዕሰ-ጉዳይ የሸሪዓ ዓለማዎችና ግቦች (መቃሲድ አሽ-ሸሪዓሕ) ነው። ስለዚህ ኢጅቲሓድ ለማድረግ ስለኢጅቲሓድ ምንነት ሸሪዓዊ የአተረጓጎም ደንቦችና ለዝርዝር ሕግጋት (አህካም) ላይ ለመድረስ መሠረት የሆኑ ሸሪዓዊ የሕግ ፍልስፍና መርሆዎችን በቅጡ መገንዘብ ተቀባይነት ያለው ውጤታማ ኢጅቲሓድ ለማድረግ ወሳኝ የብቁነት መስፈርት መሆኑን ይገነዘቧል።
5. ቅንነት (ዓዳላሕ)፡- አንድ የሸሪዓ ከላይ በተጠቀሱት ኢስላማዊ የሕግና የሳይንስ መስኮችን ከማወቅ በተጨማሪ ግለሰቡ ኢጅቲሓድ ለማድረግ የተነሳዉ የሕጉን መንፈስና ዓላማ ለማሳካት በኢጅቲሓድ አማካይነት እዉነታንና ምክንያታዊነትን መሠረት በማድረግ አመለካከትንና ምግባርን ወደ ተሻለ አቅጣጫ ለመምራት መሆን ይኖርበታል። ከዚህ የቀናኢነት ሐሳብ የተለየ ግለሰባዊ ጥቅምን የሐሳብ የበላይነት ሃይማኖታዊ ወይም ቡድናዊ የበላይነት ለመጎናተፍ ከሆነ ምንም ያህል ሙጅተሒዱ በእውቀት የተካነ ቢሆንም የያዘው የተዛባ እስቤ የተሳሳተ ድምደሜ ላይ የሚያደርሰው በመሆኑ ይህ ሰው የሚያደርገው ኢጅቲሓድ ጽኑእነት የሌለው ፍሬ-አልባ ድካም ነው። ስለዚህ ቀና እሳቤ ለምሁራዊ የሸሪዓ ምርምር ወሳኝ መመዘኛ መሆኑን ይገነዘቧል። በእነዚህ መስፈርቶች ስር የሚነሱ ተዛማጅ ነጥቦችንና ሐተታ ለማግኘት የከማሊን, PRINCIPLES, ግርጌ ማስታወሻ 17, ገጽ 374-377 ይመለከቷል።

[39] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 389-390.

[40] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 387-388.

ከ*ሱናሕ* በመቀጠል የሚገኝ የሸሪዓ አስረጅ መሆኑን ይቀበላሉ፡፡[41] የእነዚህን ሊቃውንትና ከዚያ በፊት የነበረውን የባልደረቦችን የ*ታቢዑ*ንና የ*መዝሓብ* መስራቾችን አሻራ በማስቀጠል *ኢጅቲሓድ* በሸሪዓ መስክ ብቻ ሳይሆን በየትኛውም የእውቀት መስክ ላይ ሊያንሰራራ የሚገባ መሆኑ የዘመኑ የኢስላም ሊቃውንት በትጋት እየሰሩበት ያለ እና ባለድርሻ አካላት በሙሉ የምሁራዊ ንቅናቄው አካል እንዲሆኑ ጥሪ እያቀረቡበት ያለ ቀዳሚ አጀንዳ ሆኗል፡፡ በመጨረሻም የ*ኢጅቲሓድ* መንደርደሪያ ይሆኑ ዘንድ በ*መዝሓብ* መስራቾች የተቀመሩት እንደ *ቂያስ*ና *ሰድ-አዝ-ዘራኢዕ* የመሳሰሉ የሕግ መርሆዎች ራሳቸው ወደፊት ለሚነሱ አዲስ ጭብጦች ላይ የሕግ መፍትሔ ለማበጀት የትንታኔ መነሻ ይሆኑ ዘንድ የተቀረጹ እንጂ መርሆዎቹ በንድፈ-ሐሳብነት ብቻ እንዲቀሩ አይደለም፤ ስለዚህ የእነዚህ *የኢጅቲሓድ* ኃሊዮቶች (ንድፈ-ሐሳቦች) ባህርይ በራሱ *የኢጅቲሓድን* ቀጣይነትን አረጋጋጭ ነው፡፡[42]

## 2. በመዝሓብ ስር ያሉ ሙጅተሒዶች

የ*መዝሓብ* ኢማሞች በቀረጿቸው የሕግ መርሆዎችና ቀኖናዎች ላይ ተንተርሰው ዝርዝር ሕግጋትን *(አህካም)* የሚያወጡ እና ትንታኔዎችን የሚሰጡ በየዘመናቱ የተነሱ የ*መዝሓብ* ተከታይ ሊቃውንት በዚህ በሁለተኛው የ*ኢጅቲሓድ* እርከን ስር ይመደባሉ፡፡ እነዚህ *ሙጅተሒዶች* የ*መዛሒብ ሙጅተሒዶችን* የሕግ መርሆዎች ያብራራሉ ሲባል፣ ከራሳቸው የግል እሳቤ ጋር የማይጣጣም ቢሆንም እንኳ የ*መዛሒብ* ኢማሞችን አቋም በጭፍን ይከተላሉ ማለት አይደለም፡፡ በአብዛህኛው *ከመዝሓባቸው* የሕግ መርሆዎች ጋር የሚስማሙና እነዚህን የሚያብራሩ ቢሆንም ከግል አስተያየታቸው ጋር የማይጣጣሙ የ*መዝሓብ* አቋም ሲያጋጥማቸው በጭፍን የማይከተሉ እንደውም ነቅፈው የሚከራከሩ ከኢማሞቻቸው ተቃራኒ ሐሳብ ያንጸባርቁ የነበሩ *ሙጅተሒዶች* ናቸው፡፡[43] በዚህ የ*ኢጅቲሓድ* እርከን ስር ከሚመደቡ *ሙጅተሒዶች* መካከል በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል በሀነፊ *መዝሓብ* ስር ዘፈር ኢብን አል-ሁዘይሊና ሀሰን ኢብን ዚያድ በማሊኪ *መዝሓብ* ስር ኢብን ዐብድ አል-በርና አቡ በክር ኢብን ዐረቢ በሻፊዒ *መዝሓብ* ስር ኢስማዒል ኢብን የህያ አልሙዘኒ ዑስማን ተቂ አድ-ዲን ኢብን አስ-ሶላህ እና ጀላል አድ-ዲን አስ-ሱዩጢ በሀንበሊ *መዝሓብ* ስር ደግሞ ኢብን ተይሚያሕ እና ተማሪያቸው ኢብን አል-ቀይም አል-ጀውዚያ ይገኙበታል፡፡[44]

## 3. የአፈጻጸም ልዩ *ሙጅተሒዶች*

ከላይ የቀዳሚ ኢማሞች ተከታይ *ሙጅተሒዶች* የዘረጉትን የሕግ ማዕቀፍ መሰረት አድርገዉ ነገር ግን የቀደምት *ሙጅተሒዶች* ልዩ ሽፋን ያልሰጧቸውን የሕግ ጉዳዮች በዝርዝር በመዳሰስና ያላቸውን አፈጻጸም ያብራሩ ሊቃውንት በዚህ የ*ኢጅቲሓድ* እርከን ለብቻ ተመድበዋል፡፡ እነዚህ *ሙጅተሒዶች* ከ*ኢማሞች* እና በሁለተኛ ደረጃ ከተቀመጡ *ሙጅተሒዶች* የተለየ ሐሳቦች የሌላቸው ሕግጋትን በተጨባጭ ካጋጠሙ ጉዳዮች ጋር በማዛመድ የሚያብራሩና የሚያስፈጽሙ የአፈጻጸም *ሙጅተሒዶች* ናቸው፡፡[45] ከሀነፊ *መዝሓብ* እነ አቡል ሀሰን አል-ከርኺ እና አቡ-ጀዕፈር አጥ-

---

[41] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 388.

[42] ዝኒ ከማሁ.

[43] Ma'ṣūmi, *Ijtihād through Fourteen Centuries*, ግርጌ ማስታወሻ 37, ገጽ 63.

[44] KAMALI, PRINCIPLES, ግርጌ ማስታወሻ 18, ገጽ 388.

[45] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 388. ከ5ኛው እስከ 10ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ውስጥ ከአል-ገዛሊ ባለሁለት *የኢጅቲሓድ* እርከን ተጀምሮ፣ *ሙጀተሒዶች* በሸሪዓ የሕግ *ሥርዓት* እድገት ላይ ባላቸው የምሁራዊ አበርክቶ አይነት እና ደረጃ ላይ በመመርኮዝ እስከ ሰባት *የሙጀተሒድ* እርከኖችን ለይተዋል፡፡ መጸሃፋቸው እነዚህን ሰባት *የኢጅቲሓድ* ደረጃዎች የዘረዘሩ ቢሆንም ጸሀፊው በግልጽ እንዳስቀመጡት እነዚህ ከአራት ጀምሮ እስከ ስድስት የሚገኙ የሸሪዓ ሊቃውንት ያላቸው ሚና ተቀራራቢነት አለው፡፡ ስለሆነም የአንዱ ሐሳብ በሌላው ስር የሚካተትበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ እነዚህ እርከኖች፡-

*አስሃብ አት-ተኽሪጅ* (የምርጫ ምሁራን)፡- በሸሪዓ መርሆዎችና ድንጋጌዎች ላይ በቂ እውቀት ያላቸውና ለአንድ ችግር አማራጭ የሕግ መፍትሔ ሐሳቦች ካሉ ከእነዚህ እይታዎች መካከል ከነባራዊ እውነታ ጋር ተስማሚ የሆነውን መምረጥ የሚችሉ ምሁራንን የሚመለከት ነው፡፡

*አስሃብ አት-ተርጂሕ* (የምዘና ምሁራን)፡- ተዓማኒነታቸዉ አጠራጣሪ ከሆኑ የሸሪዓ አስረጂዎች መካከል ይበልጥ ተዓማኒ የሆነዉን ለመምረጥ በቂ የምዘና እዉቀት ያላቸው፣ ጠንካራውን *(ሶሂሕ)* የተሻለዉን *(ራጂሕ፣ አርጀሕ)* የጋራ አቋም የተያዘበትን *(ሙፍታ ቢሓ)* እና ደከማ የተዓማኒነት ደረጃ ያላቸውን አስረጂዎች አንዱን ከሌላው መለየት የሚችሉ ምሁራን በዚህ እርከን ስር ተመድበዋል፡፡

*አስሃብ አት-ተስሂሕ* (ገላጭ ምሁራን)፡- በአንድ *መዝሓብ* ስር ያሉ ምሁራን ከሰነዘሯቸው የተለያዩ አስተያየቶች መካከል ለአረዳድ ግልጽ *(ሷሒር)* የሆነውን ከአሻሚው *(ነዋዲር)* በመለየት *መዝሓቡን* እይታ ለተራው አማኝ አረዳድ ግልጽ እዲሆን አድርገው የሚያቀርቡ ምሁራን በዚህ እርከን ስር ይመደባሉ፡፡ *የመዝሓብ* ሊቃውንትን *ሥነ*-ጽሁፍ በማጥናት ለተማሪዎች መማሪያ ይሆን ዘንድ በየደረጃው የሚገኙና በሰፊው ማህበረሰብ ውስጥ ጥቅም ላይ ያሉ *የመዝኃብ* የ*ፊቅሕ* መማሪያ መጻህፍትን ያዘጋጁ ምሁራን በዚህ እርከን ስር ተመድበዋል፡፡

ጦሃዊ አቡል ፈድል አል-መርዋዚ እና አቡ ኢስሃቅ አሽ-ሺራዚ ከሻፊዒ፤ አቡ በክር አል-አብሃሪ ከማሊኪ እና ዐምር ኢብን ሁሰይን አል-ኺራቂ ከሀንበሊ የሕግ ት/ቤት፣ በዚህ *የሙጅተሒዶች* እርከን ስር የሚጠቀሱ ናቸው፡፡[46]

ባጠቃላይ እነዚህ *የኢጅቲሓድ* ደረጃዎች ከቀደምት የኢስላም ዘመናት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያሉ የሸሪዓ ሊቃውንት ለኢስላም እዉቀት መጎልበት በተለይ ደግሞ ለሕግ መርሆዎች *(ኡሱል)፣ ለመዝሓብና* ለዝርዝር ሕግጋት እድገት ያላቸውን የተለያየ ምሁራዊ አስተዋጽኦ ደረጃ የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ ባለንበት ወቅት በሰፊውና በተራው የዓለም ሙስሊም ማህበረሰብ ይቅርና በ*ዑለማኦ* መካከል የሰረጸው የ*ተቅሊድ* ችግር ተቀርፎ *በኢጅቲሓድ* መተካት እንዳለበት ሸሕ ወሊዩሏህ ሙሀመድ አስ-ሰንዓኒ ሙሀመድ አሽ-ሸዉካኒ አስ-ሰኑሲ እና ሌሎች ግንባር ቀደም *ዑለማኦ* ያስገነዝባሉ፡፡[47] *የኢጅቲሓድ* በር ተዘግቷል በሚል ፈሊጥ ዘመናዊውን የሙስሊም ዓለም ለቀደምቱ ኢስላም እውቀት ተገዥ እና ጥገኛ እንዲሆን የሚያደርግ መሠረተ-ቢስ አቋም *(ቡህታን አል-ዓዚም* - ትልቅ አሉባልታ) እንደሆነ ከቀደመው የኢስላም የሕግ ሊቃውንት የካበተ እውቀትና ምርምር ትምህርት ከመቅሰም ባለፈ የአሁኑ ትውልድ ለጥንቱ የእውቀት አሻራ እስረኛ እንዲሆን የሚናፈሱ የ*ተቅሊድ* አስተሳሰቦች በጥብቅ ሊወገዙ ይገባል፡፡ ለአንድ ሚሊኒየም የዘለቀው የሐሳብ ድህነትና የአዕምሮ ጥገኝነት ሊገታ እንደሚገባ በማሳሰብ የዘመኑ ኢስላም ከቀደመው ጋር ያለው ግንኙነት ትምህርትንና ልምድን የመቅሰም አንጂ የእሳቤ ጥገኝነት እንዳልሆነ ፓኪስታናዊው የኢስላም ፈላስፋ ሙሀመድ ኢቅባል በአጽንኦት ይገልጻል፡፡[48]

ከቁርአንና ከ*ሱናሕ* በቀጥታ መርሆዎችን በመንደፍ እና የሕግ ድምዳሜዎችን ከመስጠት (ቀጥተኛ ግንዛቤ ከመውሰድ) ጀምሮ ቀድሞ የሚገኘውን የሸሪዓ እውቀት በማብራራትና ንጽጽራዊ ትንታኔ በማድረግ የዘመናችን ምሁራን ተግተው ሊሰሩ እንደሚገባ ከማሊ ያስረዳሉ፡፡ በጥናትና ምርምር ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ተመራማሪዎች መምህራን እና ተማሪዎች ለቀደሙት *ሙጅተሒዶች* ጭፍን ተከታዮች ሳይሆኑ ከሰፊው የእውቀትና የተሞክሮ አሻራቸው በቂ ስልጠና በመውሰድ ለወቅቱ የሙስሊም ማህበረሰብ አዲስ የሕግ ምርምር ውጤቶችንና የሕግ አተረጓጎሞችን ማስተዋወቅ እንዲችሉ የማብቃት ስራ ሊሰራ እንደሚገባ ከማሊ ጨምረው ያሳስባሉ፡፡[49] በአቡ ዘሕራሕ አገላለጽ ደግሞ ሀቁ በቀደመው የኢስላም *ሥነ-ጽሁፍ* የቀረበው ብቻ ነው፤ ቁርአንና *ሀዲስ* ከነባሩ የተለየ አተረጓጎም ሊሰጣቸው አይችልም፤ አዲስ ምልከታዎች ሊዳብሩ አይችሉም የሚለው አመለካከት አማኞች ከሸሪዓ ምንጮች ጋር ያላቸውን ቀጥተኛ ግንኙነት የሚያቋርጥ አሳማኝ አስረጂና መከራከሪያ ሊቀርብለት የማይችል ወሰን ያለፈ ልማዳዊ እሳቤ ነው በማለት አውግዘውታል፡፡[50]

## ሠ. የ*ኢጅቲሓድ* ማሽቆልቆል እና የዘመኑ የ*ኢጅቲሓድ* ንቅናቄዎች

የሙስሊም *ሥልጣኔ ታሪክ* እያንዳንዳቸው የ*ጋራ* መገለጫዎች ባላቸው ሦስት ምዕራፎች ተከፍሎ ሊታይ ይችላል፤ አንደኛው በሕግም ሆነ በእምነት ጉዳዮች ላይ የእውቀት መሠረት የተጣለባቸው የነቢይነት ዓመታት (610-632 ዓ.ል) የበልደረቦች ዓመታት (632-661 ዓ.ል) እና የተከታዮች (ኡመያዶች) የአመራርነት ዘመናት *( ኺላፋሕ* - 661-750 ዓ.ል) እና ከዚያ በኋላ ተከትለው የመጡት ጥልቅ እና መጠነ-ሰፊ ጥናትና ምርምር የተደረገባቸውን ሁለት የ*ኢጅቲሓድ* ምዕተ-ዓመታትን (750-950 ዓ.ል) ይይዛል፡፡[51] በእነዚህ ጊዜያት የሸሪዓ ምንጮችን መሠረት በማድረግ *ዑለማኦ* እና ተማሪዎቻቸው ያልተገደበና በነጻ እሳቤ ላይ የተመሠረተ ጥናት እና ምርምር ያደርጉ ነበር ይህም በእጅጉ ይበረታታ ነበር፡፡[52] በወቅቱ ሰፍኖ የነበረው ነጻ የጥናትና የምርምር ምህዳር በውጤቱ ውስብስብ የሐሳብ ልዩነቶች እና ቡድኖች የፈጠረ በመሆኑ የኢስላም እውቀት ተገማች እንዲሆንና ብዝኃነቱ የሙስሊሞችን አንድነት ይፈታተናል

---

በመጨረሻም ከላይ ከተዘረዘሩት ተቀራራቢ ሚና ካላቸው ምሁራን በተለየ በከማሊ መጽሃፍ ውስጥ በሰባተኛ ደረጃ የተጠቀሱት ምንም ዓይነት ምሁራዊ የሕግ ምዘና ማድረግ የማይችሉ ተራ አማኞች (ሙቀሊዱን) ናቸው፡፡ (Kamali, Principles, ግርጌ ማስታወሻ 18, ገጽ 388-390 ይመለከቷል፡፡)

[46] ዝኒ ከማሁ.

[47] ዝኒ ከማሁ ገጽ 389-390.

[48] ዝኒ ከማሁ ገጽ 390.

[49] ዝኒ ከማሁ ገጽ 391-392.

[50] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 390-391.

[51] KAMALI, SHARIA LAW, ግርጌ ማስታወሻ 18, ገጽ 246-247.

[52] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 169.

ከሚል *ሥጋት* በተለይም በሸሪዓ አረዳድ እና *ፊቅሕ* ድምዳሜዎች ላይ የነበረውን መጠነ-ሰፊ የአቋም ልዩነቶች *የጋራ* የሚያደርጓቸውን መሠረታዊ ነጥቦች መሠረት በማድረግ ከግለሰባዊ እይታነት ባለፈ ተመሳሳይ አቀራረብ እና እይታ ባላቸው ልዩ ልዩ የሕግ እሳቤ ት/ቤቶች *(መዛሒብ)* ስር እንዲካተቱ ሆኗል፡፡[53]

ሁለተኛው የሥልጣኔ ምዕራፍ እ.ኤ.አ ከ1500 በኋላ የ*ተቅሊድ* (የጭፍን ተካታይነት) ባህል በልዩ ልዩ ታሪካዊ ምክንያቶች በዓለም ሙስሊም ማህበረሰቦች እየተስፋፋ መጥቶ በመጨረሻ ስር-የሰደደ የእሳቤ ባህል እና የዓለም ሕዝበ-ሙስሊም (*ሑማሕ)* መገለጫ ሆኗል፤ በውጤቱም በመጀመሪያው የታሪክ ምዕራፍ ከታየው በተቃራኒ *ኢጅቲሓድና* ፈጠራዊ እሳቤዎች በእጅጉ እየተዳከመ መጥቶ የ*ሑማው* የውድቀት እና የእሳቤ ቀውስ (Thought Crisis) ዋነኛ መንስኤ ለመሆን ችሏል፡፡[54] ይህ እስካለንበት ጊዜ ድረስ የዘለቀው የሸሪዓ እድገት እና የ*ሑማው* የሥልጣኔ ምዕራፍ የ*ተቅሊድ* ዘመናት እየተባሉ ይጠራሉ፡፡[55]

ሦስተኛው የታሪክ ምዕራፍ በ20ኛው ክፍለ-ዘመን መጀመሪያ ላይ በጀማል አድ-ዲን አል-አፍጋኒ እና ተማሪዎቻቸው ሙሀመድ ዐብዱሕ እና ሙሀመድ ረሺድ ሪዷ[56] ፊት-አውራሪነት *ኢጀቲሓድ* እንዲያንሰራራና የዓለም ሙስሊም ማህበረሰብ ካለበት የ*ተቅሊድ* አዘቅትና የእሳቤ ቀውስ ወጥቶ ወደ ነጻ አስተሳሰብ እና ፈጠራዊ ምልከታዎች እንዲመለስ የተደረገ ጥሪና ንቅናቄ ነው፡፡ ይህ የተሃድሶ መሪዎች ጥሪ በተከታዮቹ ዐስርተ-ዓመታት ጊዜ ውስጥ በክፍለ-ዘመኑ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነትን ለማግኘት ችሏል፡፡[57] ይህ የዘመናችን የ*ኢጅቲሓድ* ጥረት ቀደም ሲል ለግማሽ ሚሊኒየም ያህል ስር ሰዶ የዓለም ሙስሊም ሕብረተሰብ የማንነት መገለጫ እስከመሆን የደረሰውን የጭፍን እሳቤ ባህል መገርሰስ ባይችልም በዓለም ዙሪያ በሚገኙ ኢስላማዊ የትምህርት ተቋማትና ጸሃፍት አማካይነት የማይናቅ የአስተሳሰብ ለውጥ እያስመዘገበ የሚገኝ እና ወደፊትም መጠነ-ሰፊ የሥልጣኔ (የእሳቤ) ተሃድሶ *(ተጅዲድ ሀዷሪ)* ማሳካት በሚችልበት ጎዳና እየተራመደ መሆኑን መናገር ይቻላል፡፡

ከ*ኢጅቲሓድ* አኳያ የአጠቃላይ የሙስሊሙን ታሪካዊ ጉዞ ከላይ በሦስት ጥቅል ምዕራፎች ተመድቦ እንደሚታይ ካየን ዘንድ በዚህ ታሪካዊ ዳራ መንደርደሪያነት ለ*ኢጅቲሓድ* መዳከም እና ለ*ተቅሊድ* እሳቤ በር የከፈቱ ምክንያቶችን እንመልከት፡፡ *በኢጅቲሓድ* ዘመናት ከሰፊዉ ሕዝበ-ሙስሊም የግንዛቤ አቅም አንፃር ተገማች ባልሆነ ከአስተማሪነቱ ይልቅ ግራ-አጋቢነቱ አመዝኖ የነበረውን ልዩነት *(ኢኽቲላፍ)* እና ብዝኃነት መልክ ለማስያዝ በሚል ዓላማ የተደራጁት *መዝሓቦች* የተመሠረቱበትን ዓላማ በሳተ መንገድ ባለንበት *የተቅሊድ* ዘመን *መዝሓቦች* ጥያቄ ወይም ተቃራኒ ሐሳብ የማይቀርብባቸው የማይተቹ አይነኬ እንደሆኑ ተደርገው ቀርበዋል፡፡ የሙስሊም ሥልጣኔ እየተዳከመ መጥቶ

---

[53] ዝኒ ከማሁ.

[54] See: Taha J. Alwani, *The Crisis of Thought and Ijitihad*, 10(2), THE AMERICAN JOURNAL OF ISLAMIC SOCIAL SCIENCES, 234 (1993).

[55] KAMALI, SHARIA LAW, ግርጌ ማስታወሻ 8, ገጽ 169.

[56] ጀማል አድ-ዲን አል-አፍጋኒ (1897 አልፈዋል) የ19ኛዉ ክፍለ-ዘመን ዓለም-አቀፍ የሙስሊም ተሃድሶ ንቅናቄ አባት ሲሆን፣ በአንድ በኩል በሙስሊሙ ዓለም ላይ ተጭኖ የነበረውን ምዕራባዊ ቅኝ-አገዛዝ እና መጤ ርዕዮተ-ዓለም በጥብቅ ሲቃወም፣ በሌላ በኩል በሙስሊሙ ዓለም ላይ የታየውን የእሳቤ እና የሥልጣኔ ውድቀት ለማንሰራራትና ወደ ቀደመው የሥልጣኔ አሻራ ለመመለስ ከጭፍን ተከታይት (ተቅሊድ) የተላቀቀ ነጻ እሳኔ በማዳበር አመክንዮን ከመለኮታዊ ራዕይ ጋር በማስታረቅና በማጣጣም፣ ሥር-ነቀል ለውጥና ተሃድሶ ለማምጣት ምሁራዊ እና የትግል መሰረት የጣለ ሊቅና ፖለቲከኛ ነበር፡፡ የአፍጋኒ ሃዋሪያት የነበሩት እና በእሱ እግር በመተካት ምሁራዊ የተሃድሶ ንቅናቄውን ያስቀጠሉት፣ ግብጻዊው ሙሀመድ ዐብዱሕ (d. 1905 አል.)፣ ሁለቱም ተሰደው በሚኖሩበት ፈረንሳይ ፓሪስ ‹አል-ዑርዋት አል-ውስቃ› (ታማኟ ገመድ) የተሰኘች ምሁራዊ መጽሔት በማዘጋጀት የእሳቤና የሥልጣኔ ተሃድሶ እሳቤዎቻውን ያስተጋቡ ነበር፡፡ ከዚህ መጽሔት በመነሳት የአፍጋኒንና የዐብዱሕን ፋና በመከተል ነቅናቄውን ያስቀጠለው ሊባኖሳዊው ሙሀመድ ረሺድ ሪዷ (d. 1935 አል.) ሲሆን ከመምህራቸው ዐብዱሕ ጋር በመሆን ‹አል-መናር› የተሰኘ የተሰኘ የምርምር መጽሔት ለሕዝበ-ሙስሊሙ ተደራሽ በማድረግ፣ የአዲስ እሳቤ (ኢጅቲሓድ) ባህል እንዲያንሰራራ ጥሪ በማድረግ የሥልጣኔ ተሃድሶ እና የሙስሊም አንድነት፣ እንዲሁም ጸረ-ቅኝ አገዛዝ ፖለቲካዊ እሳቤዎችን በማሰራጨት ዘመነኛው የሙስሊም ንቅናቄያቸው ዓለም አቀፋዊ ገጽታ ለማግኘት ችሏል፤ እንዲሁም በ20ኛው እና ባለንበት የ21ኛው ምዕተ-ዓመት መጀመሪያ ላይ በሙስሊሙ ዓለም ዙሪያ በሥነ-ትምህርት እና የኢጅቲሓድ ንቅናቄ ረገድ ለተመዘገበው የማይናቅ የእሳቤ ለውጥና ተቋማዊ የምርምር የተሃድሶ አንቅስቃሴዎች መሠረት ለመሆን ችሏል፡፡ (JUAN E. CAMPO, ENCYCLOPEDIA OF ISLAM, 5-6 (NEW YORK:FACTS ON FILE INC, 2009). SEE ALSO: NIKKI R KEDDIE, "AFGHĀNĪ, JAMĀL AL-DĪN" IN THE *OXFORD ENCYCLOPEDIA OF THE ISLAMIC WORLD* http://www.oxfordislamicstudies.com/article/opr/t236/e0022 (Oxford *Islamic Studies Online*, (Accessed፡ Feb 1, 2020).

[57] See: Taha Jabir al-Alwani, *Taqlid and Ijtihad*, 8(1) THE AMERICAN JOURNAL OF ISLAMIC SOCIAL SCIENCES, 129-130 (1991).

በምዕራባዊ ሥልጣኔ እስከተተካበት እስከ 1500 (እ.አ.አ) ድረስ ሙስሊም ምሁራን የወቅቱንና የቦታውን ተጨባጭ እውነታዎች በማገናዘብ የሸሪዓ ሕግ ልዩ ልዩ የማህበረሰብ ጥያቄዎችን እንዲመልስ እና ችግሮችን እንዲፈታ ለማድረግ ችለዋል፡፡[58] *ኢጅቲሓድ* ባሽቆለቆለበት የ*ተቅሊድ* ዘመናት እና የምዕራባውያን አዲስ ሥልጣኔ መስፋፋት ከጀመረባቸው ዓመታት ጀምሮ የቀደምት ኢስላማዊ እሴቶችንና ተቋማትን ለመጠበቅ ሲባል ሙስሊሞች የቀድሞውን የምሁራን እውቀት አሻራ እንደ ገድል ወይም ቀጥተኛ መለኮታዊ ምንጭ እንዳለው ቅዱስ መጽሃፍ ሁሉ አይነኬ አድርገው መቁጠር ጀመሩ፡፡ በመሆኑም የ*ተቅሊድ ዑለማኦ* ፈጠራዊ የሕግ ምርምር በማድረግ የወቅቱን እና የማህበረሰቡን የሥልጣኔ ደረጃ መሠረት ያደረገ አዲስ የእውቀት አተያይ እና ጭማሬ ከማድረግ ይልቅ ቀድመው የተጻፉ ድርሰናትን በማብራራት በማጠናቀር እንዲሁም የሕዳግ እና የግርጌ አጭር ማብራሪያዎችን በማዘጋጀት ላይ ብቻ ተወስኖ ቆይቷል፡፡[59]

በዓለም ዙሪያ ያለው የሙስሊም ሕብረተሰብ በአውሮፓ ቅኝ አገዛዝ ስር መውደቁን ተከትሎ የ*ተቅሊድ* እሳቤ በይበልጥ ተጠናክሯል፤ ለምዕራባዊ-ቁሳዊ የሕይወት ፍልስፍና እሴቶች ባህል እና ተቋማት ተገዥ ላለመሆን ሲባል የወግ አጥባቂነት አመለካከት የፈጠራ እና የተሃድሶ እሳቤዎችንና እንቅስቃሴዎችን በጥርጣሬ አይን የማየት እና አሉታዊ ምላሽ የመስጠት አዝማሚያዎች በይበልጥ እንዲጠናከሩ ምክንያት ሆኗል፡፡ ያም ሆኖ ቅኝ ግዛቱ ከነበረው የከረረ ተጽእኖ የተነሳ የሕግ የትምህርት እና ሌሎች የሙስሊም ሥልጣኔ ውጤቶች እና ተቋማት መልካቸውን እንዲቀይሩ ምክንያት ሆኗል፡፡[60]

ሙስሊም ሃገራት ከቅኝ-ግዛት ነጻ ወጥተው በሕገ-መንግስታዊ ሥርዓት በተደራጁበት በዚህ ጊዜም ቢሆን ምክር-ቤታዊ የሕግ አወጣጥ ቀዳሚ ሚና የያዘበት በመሆኑ የ*ኢጅቲሓድ* ሚና ከበፊቱም የበለጠ ሚና-የለሽና የማይታይ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ሃገራቱ ከዚህ ቀደም የተዳከመውንና በመጀመሪያው የሥልጣኔ ምዕራፍ የተገደበውን *ኢጅቲሓዳዊ* ምርምር ተቋማዊ ቅርጽ አግኝቶ በአዲስ መልክ እንዲያንሰራራ ማድረግ ሲችሉ ምዕራባዊ ሕጎችን በጅምላ በመኮረጅ የሃገራቸው የሕግ-ሥርዓት አካል አድርገዋል፡፡[61]

*ለኢጅቲሓድ* መዳከም ሌላኛው ምክንያት ከራሱ ከ*ኢጅቲሓድ* ዘዴ ወይም አቀራረብ ድክመት *ጋር* ይያያዛል፡፡ *ኢጅቲሓድ* በአቀራረቡ የቀደምት *ኡሱል* ምሁራን እንዳስቀመጡት ማሻሻያና ለውጥ ሳይደረግበት እስካሁን ድረስ በወረቀት ላይ ይገኛል፡፡ *ታዲያ ኢጅቲሓድ* የ21ኛው ክፍለ-ዘመን ማህበረሰባዊ ችግሮችን መፍታት እንዲሁም ነባራዊ እውነታዎችን ማገናዘብ በሚችልበት አዲስ አቀራረብ እንደገና ሊቃኝ እንደሚገባ ከማሊ ያስገነዝባሉ፡፡ የ*ኢጅቲሓድ* መርሆዎች ከሞላ ጎደል ማሻሻያና ለውጥ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡ ይህም አዲስ ምሁራዊ የሕግ ምርምርን የሚጠይቅ በመሆኑ ሃገራት ወይም ማህበረሰቦች ነባሩን *የኢጅቲሓድ* አሻራ በማስቀጠል ሸሪዓ የወቅቱን ሕብረተሰባዊ ግንኙነቶች መግዛት እንዲችል መደረግ ይኖርበታል ከመባሉ በፊት መጀመሪያ *የኢጅቲሓድ* ዘዴ እና መርሆዎች በወቅቱ እይታ ሊታረቁ ይገባል፡፡ በዚህም መሠረት *ኢጅቲሓድ* የዘመናዊው ማህበረሰብ የሕግ መሳሪያ መሆን ይችል ዘንድ ሊሻሻሉ ከሚገቡ ነጥቦች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

ምሁራን በግለሰብ ደረጃ ከሚያደርጉት *ኢጅቲሓድ* ጎን ለጎን የሕብረት *ኢጅቲሓድ (ኢጅቲሓድ ጀማዒ)* እውቅና ተሰጥቶት በስራ ላይ ሊውል ይገባል፡፡ *ኢጅቲሓድ* ከቁርአናዊው የምክክር *(ሹራ)* መርሆ *ጋር* ተጣምሮ በሕብረት የሚደረግበትን ሥርዓት መዘረጋት አስፈላጊ የሚያደርገው ከጥንታዊ በዘመናዊ ማህበረሰብ ውስጥ ውጤታማ የሆኑ ገዢ ሕግጋትን ለመቅረጽ በተለያዩ የእውቀት መስኮች ባለሙያ የሆኑ ምሁራንን አስተዋጽኦ እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡ አንድ *ሙጅተሒድ* በሁሉም ሃይማኖታዊ እና ዓለማዊ ሳይንሶች የእውቀት ባለቤት ለመሆን ስለማይችል ልዩ ልዩ ማህበራዊና የተፈጥሮ ሳይንስ ልሂቃንና ባለሙያዎች በአንድ የ*ሹራ* መድረክ ላይ በመሆን ምክክር ማድረግ

---

[58] KAMALI, SHARIA LAW, ግርጌ ማስታወሻ 8, ገጽ 171.

[59] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 169-170.

[60] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 170, See also: MUHAMMAD FADIL AL-JAMALI, ISLMIC EDUCATION, THE DIFFERENT ASPECTS OF ISLAMIC CULTURE, THE INDIVIDUAL AND SOCIETY IN ISLAM, (ed. A. Bouhdiba et al.), 177-178 (UNESCO PUBLISHING, 1998).

[61] ዝኒ ከማሁ.

የሚችሉበት ተቋማዊ ቅርጽ በማደራጀት *ኢጅቲሓድ* ለዘመናዊ የመንግሥት አወቃቀር እና የሕግ አወጣጥ እና የፍትሕ ሥርዓት አግባብነት እንዲኖረው እና ሚናው ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ ይቻላል፡፡[62]

*ኢጀቲሓድ* በቀደሙት ዘመናት በግለሰብ ሊቃውንትና *መዝሓቦች* ሲተገበር የኖረ እና ተቋማዊ ቅርጽ ያልተላበሰ ስለነበር እድገቱን እና ገጽታዎቹን እንደያዘ ለዘመናዊው ማህበረሰብና የፍትሕ አስተዳደር ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለሆነም የቅርጽ ለውጥ ሊደረግበትና በግለሰቦች *ኢጅቲሓድ* አማካይነት ይፈጸም የነበረው የሸሪዓ ሕጎችን የመቅረጽና የመተርጎም ሚና በዘመናዊው የመንግሥት አወቃቀር ውስጥ በሕግ አውጪ አካላት (የሕዝብ ተወካይ ፓርላማዎችና ምክር ቤቶች) እና የተደራጀ ተቋማዊ ቅርጽ ባላቸው የፍርድ ቤት ሥርዓት አማካይነት ነው፡፡ የሸሪዓ ሕግ በዘመኑ ሉዓላዊ መንግሥት እውቅና በተሰጠው እንዲፈጸም በተፈቀደለት መጠን *ኢጅቲሓድ* እና *ኢጅማዕ* ተፈጥሯዊ ሚናውን መጫወት እንዲችል እንደ ኢቅባል አገላለጽ ደግሞ የማህበረሰቡ የለውጥ መሣሪያ ሊሆን የሚችልበት ብቸኛው መንገድ እንደ ፓርላማዊ የሕግ አወጣጥ እና ተቋማዊ የዳኝነት ሥርዓት ሁሉ ተቋማዊ ቅርጽ ሲሰጠው ነው ይላሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከሸሪዓ ውጪ በሌላ የእውቀት መስክ የሰለጠኑ ምሁራን እና የልዩ እውቀት ባለቤቶች የሸሪዓ ምንጮችን እና *የኢጅቲሓድ* ዘዴዎችን በበቂ መጠን እስከተገነዘቡ ድረስ *ኢጅቲሓድ* ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፤ ምክንያቱም የሕግ ምሁራን ሁሉንም የእውቀት መስክ በጥልቀት አጥንተው የሕግ ቁጥጥር የሚያስፈልጋቸውን እና የሕግ ክፍተት ያለባቸው የግንኙነት ዘርፎች ለይተው ሕግ ማርቀቅ ወይም ተገቢ የሕግ ትርጉምና አፈጻጸም *(ኢጅቲሓድ)* ማድረግ አይችሉም፡፡ ቢያንስ በሌሎች ሳይንሶች የካበተ እውቀት ያላቸው ምሁራን *ኢጅቲሓድ* ለማድረግ በቂ የሸሪዓ ግንዛቤ እስኪጨብጡ ድረስ እና የትምህርት ሥርዓቱም ይህን ታሳቢ ያደረገ ተሃድሶ እስከሚደረግበት ድረስ[63] የሕግ ምሁራን እና ሌሎች ባለሙያዎች *በኢጅቲሓድ-ጀማዒ* ውስጥ ሆነው ተደጋግፈው *ኢጅቲሓድ* ማድረግ የሚችሉበት ተቋማዊ ማዕቀፍ ሊዘረጋ ይገባል፡፡[64]

ግልጽ የሆነ የቁርአን ወይም የ*ሱናሕ* ድንጋጌ ባለበት *ኢጅቲሓድ* የለም *(ላ ኢጅቲሓድ ዐለ ኣን-ነስ)* የተሰኘው የሸሪዓ ሕግ ቀኖና *(ቀዋዒድ ኣል-ፊቅሕ)*[65] እንደገና ሊቃኝና ግልጽ እና ትርጉም የማያስፈልጋቸው የሚመስሉ ድንጋጌዎች ከሁኔታው መለወጥ ጋር ሊለወጡ የሚችሉበት በተለይ ከመጀመሪያው ሕግጋቶቹ ሲወጡ ሁኔታውን ታሳቢ በማድረግ መሆኑን በመገንዘብ ሁኔታው ሲቀየር ሕጉ ግልጽ ቢሆንም አብሮ ሊለወጥ የሚገባ መሆኑን በማመን ቀኖናው ሊታረም ይገባል፡፡ ሕጉ መለኮታዊ ምንጭ ካለው እና ግልጽ እስከሆነ ድረስ በየትኛውም ሁኔታ ሊለወጥ አይችልም የሚለው የእምነት እሳቤን የተከተለ እንጂ የሕግ ባህሪን የተከተለ አይደለም፡፡ አምላክ ራሱ የሁኔታዎችን መለወጥ ተከትሎ የለወጣቸው የሻሯቸው የሸሪዓ ሕግጋቶች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ጥቂት የተሻሩ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ባይደረጉም በቁርአን ውስጥ ያልተወገዱና ተነባቢነታቸው ቀጥሎ እናገኛለን፡፡ ከኢስላም በፊት ባሉት አምላካዊ ሃይማኖቶች ውስጥ የነበሩት መለኮታዊ ድንጋጌዎች ከቁርአን መውረድ ጋር መሻራቸው በራሱ የሕግ መሻሻልና ለውጥ መለኮታዊ ወይም ሰብዓዊ ከመሆን ጋር የተያያዘ ሳይሆን ከሁኔታዎች መለወጥና ከማህበረሰቡ ተጨባጭ ጋር የሚራመድ ባህርይ ያለው መሆኑን እንረዳለን፡፡ በዚህም መሠረት በቁርአን እና በ*ሱናሕ* ውስጥ የተካተቱ ድንጋጌዎች

---

[62] Aznan Hasan, *An Introduction to Collective Ijtihad (Ijtihad Jama'i): Concept and Applications,* 20(2) THE AMERICAN JOURNAL OF ISLAMIC SOCIAL SCIENCES, 32-33 (2003).

[63] ተቅሊድን ለማስወገድና ኢጅቲሓድን ለማንሰራራት በአውሮፓ ቅኝ-አገዛዝ ምክንያት የሰፈነው የሁለትዮሽ የትምህርት ሥርዓት *(Educational Dualism)* ሊወገድ እና በምትኩ መለኮታዊ የእውቀት ማዕቀፍ ስር (Tawhidic Epistemology) የሆነ አሃዳዊ የእውቀትና የትምህርት ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ ይህ የዘመኑ የኢስላም ሊቃውንት ምሁራዊ እንቅስቃሴ ‹እውቀትን ኢስላማዊ ማድረግ› *(Islamization of Knowledge)* ይባላል፡፡ (Rosnani Hashim & Imron Rossidy, *Islamization of Knowledge: A Comparative Analysis of the Conceptions of AI-Attas and AI-Faruqi,* 8(1) INTELLECTUAL DISCOURSE, 20-22 (2000)). በኢስላማዊ የሥርዓት-ትምህርት ቀረጻ መሠረት መሠረታዊ የኢስላም ሳይንሶች በየትኛውንም የሳይንስ መስክ ጥናት ውስጥ ተካተው እንደ አይቀሬ የትምህርት አይነት (Core Courses) ሆነው ይቀርባሉ፡፡ ለምሳሌ በጤና መስክ ለሚቀረጸው የሕግ ፖሊሲ እና ዝርዝር ድንጋጌዎች የመስኩ ተማሪዎች መሠረታዊ የሸሪዓ ሕግ ጥናት (ኡሱል አል-ፊቅሕ እና ፊቅሕ) የሚሰጣቸው በመሆኑ በመስካቸው ኢጅቲሓድ ለማድረግ መሠረታዊ የሕግ ትንታኔ ዘዴ ይጨብጣሉ፡፡ ይህ እውን መሆን የሚችለው በግለሰብ ደረጃ ከሚደረገው ጥረት ባሻገር ሥርዓት-ትምህርቱ በይዘቱም ሆነ በአቀራረቡ የዘመኑ የሥነ-ትምህርት ሊቃውንት እንደሚያስተምሩት አስፈላጊው ማሻሻያና ለውጥ ሲደረግበት ነው፡፡

[64] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 164-170.

[65] አልዩ አባተ ይማም፣ ሦስተኛው የሸሪዓ ምንጭ፣ አመክንዮኣዊ የሕግ ምርምር (ኢጅቲሓድ):- ምንነቱና መገለጫዎቹ፣ 11 JIMMA UNIVERSITY JOURNAL OF LAW, 88 (Dec. 2019) ይመለከቷል፡፡

ግልጽ *(ቀጥዒ)* ቢሆኑም እንኳ እንዳሉ ተፈፃሚ ማድረግ ከሕግ ዓላማና መንፈስ አኳያ ቀልባሽ ውጤት የሚኖረው ከሆነ እንደ ሁኔታው ሕጉን ወይም አፈጻጸሙን ማገድ ወይም መለወጥ *(ኢስቲህሳን)* ሊያስፈልግ ይችላል።[66]

*ከተቅሊድ* ዘመናት በፊት በነበረዉ ሰፊ *የኢጅቲሓድ* ልዩነት እና የሕግ እሳቤ ብዛኃነት አንጻር እንዲሁም ይህን ተከትሎ በመጣው የቡድን ተገዢነት እና ጭፍን ተከታይነት ችግር የተነሳ የዘመናችን *የፊቅሕ* ምሁራን እና ተከታዮቻቸው *የመዝሓብ* ወገንተኝነት ችግር ስር የሰደደበት ጊዜ ላይ እንገኛለን። *ኢጅቲሓድ* ተዳክሞ *በተቅሊድ* መተካቱ ሳያንስ፣ የተለያየ የሸሪዓ አቋሞችና ብዝኃነት የማያስተናግድ የሕግ ምህዳር ተፈጥሯል። ከመነሻው የተለያዩ *መዝሓቦች* ሊፈጠሩ የቻሉበት ምክንያት በነጻ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ *የኢጅቲሓድ* ምህዳር በመጀመሪያዎቹ የኢስላም *ሥልጣኔ ታሪክ* ላይ የነበረ በመሆኑ ነው።[67] የዚህ ውጤት የሆነው በርካታ *መዝሓቦች* እና ግለሰባዊ አቋሞች መፈጠራቸው ነው። በሸሪዓ *መዝሓቦች* መካከል ያለው ልዩነት ካላቸው የሀዲስ ዘገባ ተደራሽነት መለያየት ወይም *የኢጅቲሓድ* አቀራረብና መርሆዎች መለያየቱን ተከትሎ የሚመጣ የአተረጓጎም ልዩነት ነው። ባለንበት ዘመን *የኢጅቲሓድ* ሚና *ኡሱል*ን መሠረት ባላደረገ የሕግ አረዳድ ወይም ምንጮችን *(ሀዲስን)* ካለማግኘት የተነሳ የተፈጠሩ የአረዳድ ልዩነቶች ማጥበብ በሚችልበት አቅጣጫ እንዲራመድ ማድረግ ያስፈልጋል። ስለዚህ የዘመኑ *ኢጅቲሓድ* ያሉትን የሱኒ እና የሺዓ *መዝሓቦች* እና ግለሰባዊ አቋሞች ወደ አንድነት የሚያጠናቅር መሆን አለበት። በርግጥ ተገቢ የሆኑ *የኢጅቲሓድ* ልዩነቶች ሊጠበቁና በዚህ ረገድ ያለው ብዝኃነት በሸሪዓው የተደገፈና የሚበረታታ መሆኑ ይገነዘቧል፡ ፡

በቀደሙት ጊዜያት *ኢጅቲሓድ* በዋናነት የሕግ ምርምር ውስጥ ትርጉም የሚሰጥበት ወይም አዳዲስ ድንጋጌዎች የሚቀረጹበት መሳሪያ እንጂ በሌሎች የሳይንስ መስኮች ውስጥ የሸሪዓ ምንጮች (ቁርአን እና *ሱናሕ)* ያላቸው ሳይንሳዊ ድምዳሜና አንድምታ መመሪያ መሳሪያ ሆኖ ጥቅም ላይ አልዋለም። *ኢጅቲሓድ ከፊቅሕ* ማዕቀፍ ውጪ ለየትኛውም ማህበረሰባዊ ችግር መፍቻ ቁልፍ መሆኑ ታውቆ የኢስላም እውቀት ምንጮች ለሌሎች ማህበራዊና ተፈጥሯዊ ሳይንሶች ያላቸው አበርክቶ የሚፈተሽበት ዘዴ መሆኑ በተግባር ሊረጋገጥ ይገባል። ይህም እውቀት ኢስላማዊ ማድረግ *(Islamization of Knowledge*) የተሰኘውን ታላቅ የክፍለ-ዘመኑን የምሁራን እንቅስቃሴ የሚመለከት ነው።[68]

## ረ. ኢጅቲሓድ እና ዘመነኛ የሸሪዓ ጭብጦች

የዘመኑ *ኢጅቲሓድ* ለቀደመው *የኡሱል* እና *የፊቅሕ* ሊቃውንት *የኢጅቲሓድ* አሻራ ተገዢ እና ጭፍን ተከታይ መሆን የለበትም የሚለው እና ‹*የኢጅቲሓድ* በር ተዘግቷል› የሚለው ብሒል መቀየር እንዳለበት እና አዲስ *ኢጅቲሓድ* ንቅናቄ በዓለም ዙሪያ ሊጀመር እንደሚገባ ጥሪ ያቀረቡት የክፍለ-ዘመኑ የተሃድሶ መሪዎችና የሸሪዓ ሊቅ የሆኑት እነ ጀማል አድ-ዲን አል-አፍጋኒ እና ተማሪዎቻቸው ሙሀመድ ረሺድ ሪዷ እና ሙሀመድ ዓብዱሕ ናቸው።[69] በተለይ ደግሞ ከሉላዊነት ባህሪ *(Globalization) ጋር* ተያይዞ የዘመኑ የኢኮኖሚ ማህበራዊ እና ባህላዊ እውነታ በፍጥነት የሚለዋወጥ ከመሆኑ ጋር ለቀድሞ የሸሪዓ ብይኖች ተገዥ መሆን ይቅርና፣ ለውጡን የተከተለ ፈጣን *የኢጅቲሓድ* ክንውን ማድረግ ያስፈልጋል። *ኢጅቲሓድ* የሚታየውን ተለዋዋጭ ሁኔታ ገዢ መሆን እንዲችል ከማድረግ በተጨማሪ የግለሰቦችንና የማህበረሰቡን ዘርፈ-ብዙ ግንኙነቶች ለመቆጣጠርና ሁለንተናዊ የሸሪዓ ፍትሕ ለማቅረብ ይቻል ዘንድ *በኢጅቲሓድ* ተግባር ውስጥ የሸሪዓ ሕግ ምሁራን ብቻ ሳይሆኑ በልዩ ልዩ የሳይንስ መስኮች ልዩ *ሥል*ጠና እና ሙያ ያላቸው ሰዎች *የኢጅቲሓድ* አካል ሊሆኑና የእውቀት መስኮቹ የደረሱበትን የእውቀት ጥግ ለሕግ አውጪዎች በማቅረብ *ኢጅቲሓዳዊ* እንቅስቃሴ ላይ እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሰሩበት አሳታፊ *ሥ*ርዓት ሊዘረጋ ይገባል።[70] ባለንበት ዘመን

---

[66] አልዩ አባተ ይማም፣ *የሸሪዓ ሕግ ዓላማዎች (መቃሲድ አሹ-ሸሪዓሕ)፣* 7(2) BAHIR DAR UNIVERSITY JOURNAL OF LAW, 275-276 (June 2017) ይመለከቷል።

[67] አልዩ አባተ ይማም፣ (ምልከታ) የሸሪዓ እድገትና ቀዳሚ የሕግ ትምህርት ቤቶች፡ ከኢትዮጵያዊ ምልከታዎች ጋር፣ 8 HARAMAYA LAW REVIEW, 74-75 (2019).

[68] Rosnani Hashim & Imron Rossidy, *Islamization of Knowledge: A Comparative Analysis of the Conceptions of AI-Attas and AI-Faruqi*, 8(1) INTELLECTUAL DISCOURSE, 20-22 (2000).

[69] Nazeem Mi Goolam, *Ijtihad and Its Significance for Islamic Legal Interpretation*, MICHIGAN STATE LAW REVIEW, 1458-1459 (2006).

[70] KAMALI, SHARIA LAW, ግርጌ ማስታወሻ 8, ገጽ 171.

*ኢጅቲሓድ* በሦስት ዓይነት ቅርጽ ሊፈጸም ይችላል፤ አንደኛው ሸሪዓ መንግሥታዊ ሕግ በሆነበት ሉዓላዊ ሃገር ውስጥ *ኢጀቲሓድ* በሕግ አወጣጥ ሚናው በሕግ አውጪ ምክር ቤቶች ሊከናወን ይችላል። ለምሳሌ በሙስሊም ሃገሮች ባሉ ሕግ-አውጪ አካላት ከተደረጉ ተቋማዊ *ኢጅቲሓድ* መካከል የዘመኑን ሕብረተሰባዊና ግለሰባዊ ግንኙነት መሠረት በማድረግ በነባሩ የሸሪዓ ሕግ ላይ የተደረጉ *ኢጅቲሓዳዊ* ማሻሻያዎች ተጠቃሽ ናቸው። በነባር የሸሪዓ ሕጎች ላይ በዳኝነት አካላት የሚተገበር *ኢጅቲሓዳዊ* የሕግ ትርጉም ሁለተኛው ቅርጽ ሲይዝ ሦስተኛው ደግሞ በ*ኡሱል* ሊቃውንት አማካይነት በመስኩ *ሥነ-ጽሁፍ* ውስጥ የሚደረገውን *ኢጅቲሓዳዊ* የሕግ ምርምር ይመለከታል።[71]

የቀድሞው *የኢጅቲሓድ* አቅጣጫ በታወቁት የሕግ መርሆዎች ማለትም *በቂያስ፣ በኢስቲህሳን፣ በኢስቲስሃብ* ወዘተ.. ላይ ተመስርቶ የነበረ ቢሆንም አሁን ደግሞ የሸሪዓ ዓላማዎችና ግቦች *(መቃሲድ አሽ-ሸሪዓሕ)* ሰፊ ትኩረት እያገኘና *የኢጅቲሓድን* ቅርጽ በማሻሻል ላይ ይገኛል። ለዚህም ምክንያቱ ደግሞ *ኡሱላዊው የኢጅቲሓድ* አቀራረብ ለ*መቃሲድ* ከነበረው አናሳ ትኩረት የተነሳ ያሉበትን ድክመቶች በማስተዋል *መቃሲድን* መሠረት ያደረገ *ኢጅቲሓድ* በእድገት ላይ ያለ የቅርብ ዓመታት አዲስ የሸሪዓ ኩነት ነዉ። ዑበይዱላህ ሲንዲ እንደሚያስረዳው የአንድን ሕግ የድንጋጌ ምክንያትና ዓላማ ማወቅ ከልብ በመነጨ ተነሳሽነትና ባመነ መንፈስ ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላል፤[72] ይህም የግላዊ ሁኔታዎች መለዋወጥ የማይበግረው ዘላቂነት ያለው የሕግ ተገዥነት ይፈጥራል። እያንዳንዱ ትውልድ በቀደምቶች አስተሳሰብ ሳይወሰን የሚገጥሙትን አዳዲስ ሁኔታዎችና ችግሮች በራሱ እይታ መፍታት ሊፈቀድለት እንደሚገባ ሙሀመድ ኢቅባል ያስገነዝባሉ።[73] በዚህም መሠረት የ21<sup>ኛውን</sup> ክፍለ-ዘመን ሙስሊም ሕብረተሰብ ተጨባጭ እውነታ መሠረት በማድረግ በ*ኢጅቲሓድ* አማካይነት ማሻሻያ ከሚያስፈልጋቸው የ*ፊቅሕ* ድንጋጌዎችና ገጽታዎች መካከል ሙሀመድ ሃሺም ከማሊ የሚከተሉትን ዘርዝረዋል።[74]

ሴቶችን የተመለከቱ አንዳንድ *ፊቅሒ* አቋሞች፣ ለምሳሌ ሴቶች በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ በተመለከተ የሸሪዓ ትላልቅ የፍትሕ እና የእኩልነት ዓላማዎች እና ሴቶች ባለንብት ከፍለ-ዘመን ያላቸውን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሚና ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አዲስ *ኢጅቲሓድ* ሊደረግ ይገባል። ነባሩ *ፊቅሓዊ* አስተያየት ሊሻሻል ብሎም ሊለወጥ እንደሚገባ ያሳስባሉ።

ሸሪዓ ለሕገ-መንግሥታዊና ለፓርላማዊ የምክክር *(ሹራ)* የመንግሥት አወቃቀር ሕዝባዊ የመንግሥት ተሳትፎ ሰብዓዊ መብቶችና ነጻነቶች ባጠቃላይ ዲሞክራሲያዊ የአስተዳደር ሥርዓትን በተመለከተ ሸሪዓ ያለው አቋም በነባሩ የ*ፊቅሕ ሥነ-ጽኁፍ* ውስጥ ተገቢውን ትኩረት ያላገኘና በቂ *ኢጅቲሓዳዊ* ምዘና ያልተደረገበት በመሆኑ ከተንጸባረቀው ልዝብ *የፉቅሓእ* ድጋፍ በተለየ ግልጽና በማያሻማ መልኩ በ*ኢጅቲሓድ* ሊመረመር ይገባል። በተቀራኒው በሕዝብ ሉዓላዊነት ላይ ላልተመሠረተ እና ለአምባገነናዊ የአገዛዝ ሥርዓት ሸሪዓ የለው አሉታዊ አቋም በመካከለኛው የ*ፊቅሕ ሥነ-ጽኁፍ* ላይ ካለው በተለየ በምሁራን ወጥ አቋም *(ኢጅማዕ)* ግልጽ *ኢጅቲሓዳዊ* አቋም ሊንጸበረቅበት ይገባል።

*የኢጅቲሓድ* ጽንሰ-ሐሳብን በማዛነፍ ለአፍራሽ የአመጽ እና *ሥርዓት*-አልበኝነት ተግባራት ሸሪዓዊ ሽፋን ለመስጠት የሚደረጉ አተረጓጎሞችና አዝማሚያዎች ላይ *ዑለማእ ኢጀማዕ* ደረጃ የደረሰ ወጥ ሸሪዓዊ ብይን ሊሰጡበትና ይህም በስፋት ሊስተጋባ ይገባል።

በቤተሰብ የሸሪዓ ማዕቀፍ ውስጥ ከፍች እና ከአንድ በላይ ከማግባት ጋር ተያይዞ ድንጋጌዎቹ የወጡበትን የወቅቱን ማህበረሰብ ባህልና ከዚያ በኋላ በጊዜ ሂደት የተስተዋለውን ማህበረሰባዊ የአስተሳሰብ እና የመስተጋብር ለውጥ ግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ ረገድ በብዙዎቹ የሙስሊም ሃገሮች *ኢጅቲሓዳዊ* የሕግ ማሻሻያዎችን ያደረጉ ቢሆንም አሁንም የሸሪዓውን ተለማጭነትና ነባራዊነት በሚያስረግጥ መልክ ማህበረሰባዊ አስተሳሰብ እና የሕግ ባህል ለውጥን እስኪያመጣ ድረስ የመስኩ ምሁራን *ኢጅቲሓድ* ሊያደረጉበት እና እይታቸውን በተደጋጋሚ ይፋ ሊያደርጉ ይገባል።[75]

---

[71] ዝኒ ከማሁ.

[72] KAMALI, SHARIA LAW, ግርጌ ማስታወሻ 8, ገጽ 172.

[73] ዝኒ ከማሁ.

[74] ዝኒ ከማሁ ገጽ 173-174.

[75] አልዩ አባተ ይማም፣ *የሸሪዓ ሕግ፡ ምንነቱ፣ መገለጫዎቹ እና ምንጮቹ፣* 9(1) BAHIR DAR UNIVERSITY JOURNAL OF LAW, 151-152 (2017).

ክህደትና ሃይማኖትን መቀየር *(ሪዳሕ - Apostacy)* በተመለከተ በ*ሀዲስ* የተደነገገው የሞት ቅጣት አፈጻጸምን በተመለከተ ሕጉ የተደነገገበት ከባቢያዊ ሁኔታ ሲታይ እምነቱን ማስተባበል ብቻውን ቅጣቱን ተፈጻሚ እንደማያደርገው ይልቁንም የሕጉ መንፈስና ዓላማ ክህደቱን ተከትሎ በሙስሊም ማህበረሰብ ግዛትና አመራር ላይ አፍራሽ እንቅንስቃሴ የሚያደርግን ግለሰብ የሚመለከት እንደሆነ *ሀዲሱ* ራሱ አመላካች ሲሆን በቁርአን ውስጥ ክህደት በራሱ የወንጀልነት ቅርጽ ያልተሰጠው መሆኑ እንደውም በተቃራኒው የእምነት ነጻነትን የሚያረጋግጡ አንቀጾች መኖራቸው የሀዲሱን መልዕክት ግልጽ ያደርጋል። ባጠቃላይ ሃይማኖት ማስተባበልን *(Apostacy)* ጨምሮ የሸሪዓ ድንጋጌዎች ላይ የተለመደውን አሰራር የመከተል ወግ አጥባቂነት ውጪ *ኢጅቲሓድ* በማድረግ ውስብስብ ለውጦች እያስተናገደ ያለውን ማህበረ-ሰብዕ ያገናዘበ የሕግ አረዳድ ሕንድን ጨምሮ በሌሎች ሃገሮች በሚገኙ የሸሪዓ ፍ/ቤት ዳኞችና ምሁራን ሊቃውንት መካከል የሸሪዓውን ተለዋዋጭነት ያገናዘበ የሕግ ምርምር እንደማይደረግ ሕንዳዊው የኢስላም ፈላስፋ ሙሀመድ ኢቅባል ያስገነዝባል። በኢቅባል አገላለጽ የኢስላም ሕግ የማይለወጥና ለእድገት የተገራ አይደለም በሚል በኢስላም ላይ የሚሰነዘረው ትችት የሸሪዓውን *ሥነ-ጽሁፍ* በመፈተሽ የሚቀርበው ሂስና ነቀፌታ መሠረት-አልባ እንደሆነ መረዳት ይቻላል።[76]

## ሰ. ማጠቃለያ

የሸሪዓ ምንጮች በጥቅሉ ራዕያዊና አመክንዮአዊ በሚል በሁለት ሊመደቡ ይችላሉ። ራዕያዊ የሸሪዓ ምንጮች ውስጥ አንደኛው በቀጥታ ከአምላክ ወደ ነቢዩ ሙሀመድ የተገለጸውን መለኮታዊ ራዕይ ማለትም ቅዱስ ቁርአን ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ፍሬ-ሐሳባዊ ምንጬ ከአምላክ ሆኖ አገላለጹ የሙሀመድ የሆነው *ሱናሕ* ነው። ሁለተኛው የሸሪዓ ምንጭ *ኢጅቲሓድ* ሲሆን ይህም የቁርአንና የ*ሱናሕ* ምንጮችን መሠረት አድርጎ በቀጥታ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች በአመክንዮአዊ የሕግ ትንታኔ የሚሸፈኑበትን የምርምር ዘዴዎች የሚመለከት ነው። በመጀመሪያዎቹ የሸሪዓ እድገት ዘመናት የተመሠረቱት የሕግ ት/ቤቶች የተቀረጹት የ*ኢጅቲሓድ* ንድፈ-ሐሳቦች አጠቃላይ የቁርአንን የሕግ ፍልስፍና የሚወክሉ ሲሆን መርሆዎቹ ዘመንና ትውልድን ተሻግረው በየወቅቱ ለሚነሱ አዳዲስ የሕግ ጭብጦች የሕግ መፍትሔ ለማበጀት መንደርደሪያ በመሆን ያገለግላሉ። በተለይ በቁርአንና በ*ሱናሕ* ተለይተው የተቀመጡ ዝርዝር ድንጋጌዎች በቁጥር አናሳ በመሆናቸውና ቁርአንና *ሱናሕ* በዋናነት ጠቅላላ መርሆዎችን የሚያቀርቡ በመሆኑ ዘርፈ-ብዙ የሕግ ርዕሰ-ጉዳዮችን ለመግዛት ዋነኛው ሸሪዓ ምንጭ የሊቃውንት የሕግ *ኢጅቲሓድ* ሆኖ እናገኘዋለን። እንደ ቀደምት የ*መዝሃብ* መስራቾች ከቁርአንና ከ*ሱናሕ* በመነሳት ኦርጅናል የሕግ መርሆዎችንና ድንጋጌዎችን መቅረጽ የሚችል የለም የሚል እሳቤ የዓለምን የሙስሊም ማህበረሰብ ለውድቀት የዳረገ ለቀዳሚው የሸሪዓ እድገት ጭፍን ተገዥ *(ሙቀሊድ)* እንዲሆን ያደረገ እንዲሁም የሸሪዓን እድገት የገታ መሠረት አልባ የሕግ ባህል ነው። ዘመነኛ የሸሪዓ ምሁራንና የተሃድሶ መሪዎች ይህን ተጨባጭ እውነታ ለመቀየር የቀደመው የ*ኢጅቲሓድ* ባህል በሕግም ሆነ በልዩ ልዩ የሳይንስ መስኮች ላይ ያለው ከፍተኛ የምንጭነት ሚና እንዲያንሰራራ ርብርብ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ጥረቱን ተከትሎ በሙስሊም ሃገሮችና ሙስሊም ዜጎች የሚገኙባቸዉ የዓለም ሃገራት ሸሪዓን ከወቅቱ የሙስሊም ማህበረሰብ አስተሳሰብና ነባራዊ እውነታ አኳያ እያጋጠሙ ላሉ አዳዲስ ችግሮች እንዲሁም ነባሩን የሸሪዓ ሕግ ለማሻሻል ሲባል ሸሪዓዊ የሕግ ምርምር *(ኢጅቲሓድ)* በተለያየ ደረጃ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። በተለይም *ኢጅቲሓድ* የሚያደርጉ እና ወቅታዊ የሸሪዓ ጥናት የሚያደርጉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጀምሮ እስከ አስገዳጅ ወይም ምክረ-ሐሳብ የሚያቀርቡ የ*ሙጅተሒድ* ምክር ቤቶች ብሎም በሕገ-አውጪ ምክር ቤቶች ደረጃ ተቋማዊ ቅርጽ አግኝቶ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል።

በኢትዮጵያ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች የሸሪዓ የግልና የቤተሰብ ሕግ ተፈጻሚ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በዚህ ረገድ ያለውን *የመዝሓብ* ብዝኃነት እና ልዩ የሕግ አቋሞች መካከል አንዱን በመምረጥ ተፈጻሚ ለማድረግ የጠቅላላው የኢትዮጵያ የሙስሊም ማህበረሰብ ነባራዊ እውነታዎችና የቀረበላቸውን ልዩ ጉዳይ መሠረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በዳኝነት *ሥራቸው* ወቅት ለግጭት አፈታት ተፈጻሚ የሚያደርጓቸውን የሸሪዓ የፍሬ-ነገር ሕጎችና አተረጓጎማቸውን በተጨባጭ በመመርመር *ኢጅቲሓድ* ከወቅቱና ከማህበረሰቡ አኳያ የትርጉም ወይም የሕግ አወጣጥ *ኢጅቲሓድ* ሊደረግባቸው የሚገቡ ጭብጦችን በመለየት አማራጭ ሐሳቦችን ማቅረብ የዚህ ጽሁፍ ዓላማ ባይሆንም የሌላ ምርምር ርዕሰ-ጉዳይ ተደርጎ ጥናት ሊደረግበት እንደሚገባ በመጠቆም በዳኝነት *ሥራቸው* ወቅት *ኢጀቲሓድ* ሊደረግባቸው በሚገቡ ጉዳዮች

[76] KAMALI, SHARIA LAW, ግርጌ ማስታወሻ 8, pp. 173-174.

እንዲሁም በሰፊው የዓለምና የኢትዮጵያ ሙስሊም ማህበረሰብ ውስጥ እንዳለው ስር የሰደደ የ*ታቅሊድ* ባህል በፍ/ቤቶች አካባቢ ሊወገድና በዚህ ጽሁፍና በሌሎች የመስኩ *ሥነ-ጽሁፍ* በተተነተነው መልክ ሸሪዓዊ የሕግ ምርምር ሊዳብር ይገባል፡፡ አሁን ባለው የፍ/ቤቶች አሰራር የሚቀርበው ጉዳይ ላይ አዲስ *ኢጅቲሓዳዊ* የሕግ አተረጓጎሞችና አፈጻጸሞችን ማዳበር ይቅርና ጉዳዮች ዳኛው በሚከተለው *መዝሓብ* መሠረት እንደሚዳኙ የሚያስረዱ መረጃዎች አሉ፡፡[77] ይህ የዳኝነት ሥርዓት በፍ/ቤቶች መካከል ወጥነት የሌለው የሕግ አተረጓጎም እንዲሰፍን የሚያደርግና በሕብረተሰቡም ዘንድ ተገማችነት የሌለው የፍትሕ አሰጣጥ ሥርዓት እንዲሰፍን የሚያደርግ ነው፡፡

ፍ/ቤቶችና ዳኞች ከሕገ-መንግሥታዊ የሰብዓዊ እሴቶች ጋር ተጻራሪ ናቸው የሚል ስጋት በተፈጠረባቸው የሸሪዓ ቤተሰብ ድንጋጌዎች ላይ አስፈላጊውን *ኢጅቲሓዳዊ* ማሻሻያዎችን ለማምጣትና በዚህ ረገድ ወጥ የሆነ የሸሪዓ አተረጓጎም እንዲኖር ይቻል ዘንድ አንድ ማዕከላዊ የሸሪዓ *(ኢጀቲሓድ)* ምክር ቤት ወይም ብሔራዊ የ*ኢጅቲሓድ* ጥናትና ምርምር ማዕከል ማቋቋም ለችግሩ አይነተኛ መፍትሔ እንደሆነ እንደ ሱዳን፣ ማሌዥያና ፓኪስታን ያሉ ሃገሮች ተሞክሮ ያሳያል፡፡[78]

የሸሪዓ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበታች ፍ/ቤቶች ያለውን የሕግ አተረጓጎም ወጥ በማድረግ፣ እንዲሁም አስፈላጊውን *ኢጅቲሓድ* በማድረግ ማሻሻያና አዳዲስ የሕግ ምልከታዎች ሊዘርጋ የሚችል ቢሆንም ከይግባኝ በዘለለ የሰበር ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ የሚያመላክት የሕግ አንቀጽ በሸሪዓ ፍ/ቤቶች ማጠናከሪያ አዋጅ አልተመለከተም፡፡ ያም ሆኖ የበላይ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች የይግባኝ ሥልጣናቸውን በ*ኢጅቲሓድ* የተመራ የሕግ አተረጓጎሞችን በመከተል ተግባራዊ ካደረጉት የሰበሩን ያህል የአስገዳጅነት ደረጃ ባይኖረውም ሸሪዓ ሕጉን ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣምና የዳኞች *የታቅሊድ* እሳቤዎችን በማረም እንዲሁም ወጥ አተረጓጎም በማስፈን ረገድ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

በተጨማሪም በሸሪዓ ፍ/ቤቶች ሊኖር የሚገባው *ኢጅቲሓድ* እንቅስቃሴ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሸሪዓ ጥናትና ምርምር ሊታገዝ ይገባል፡፡ በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ውስጥ ሸሪዓ ሕግ የነበረው ድርሻ የየማህበረሰቡን የግልና የቤተሰብ ግንኙነት እንዲገዛና በዚህ ረገድ የሚነሱ ግጭቶች በሕጉ አማካይነት እንዲዳኙ ካገኘው አስገዳጅ ሕገ-መንግሥታዊ እውቅና በተጨማሪ መንግሥት የሙስሊሙን የወለድ-ነጻ የባንክ አገልግሎት ፍላጎት ለማርካት የተከተለውን አበረታች ውሳኔ ተከትሎ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በ2011 (እ.ኤ.አ) ባወጣው መመሪያ መሠረት[79] በሃገሪቱ እየሰሩ ያሉ ንግድ ባንኮች የወለድ ነጻ አገልግሎት እንዲያቀርቡ የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ በመመርያው በግልጽ እንደተመለከተው የባንክ ሥራውን በመምራት እና በመቆጣጠር ተፈጻሚ የሚሆኑት ኢስላማዊ የፋይንስ ሕጎችና ወጥ አስራር ደንቦች እንደሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይህም ሸሪዓ በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ተፈጻሚ የሚሆንበትን ወሰን አስፍቶታል፡፡ ወደፊትም የዘርፉን እድገት ተከትሎ የተፋጻሚነት ወሰኑ እየሰፋ እንደሚሄድ መገመት ይቻላል፡፡ ቤተሰባዊ ግኙነቶችን እና ኢስላማዊ የባንክ ግብይቶችን የሚገዛው የሸሪዓ ሕግ ዋነኛ ምንጬ ብቁ የዘርፉ ምሁራን የሚያደርጉት የአመክንዮኣዊ የሕግ ምርምር ወይም *ኢጅቲሓድ* እንደሆነ በዚህ ጽሁፍ አጽንኦት ተሰጥቶታል፡፡ ታዲያ የሸሪዓ የፍርድ ሥርዓቱን የወለድ-የባንክ ሥራውን በማጠናከር በማሻሻል እና በማስፋፋት ረገድ *ኢጅቲሓድ*ና ሌሎች የሸሪዓ ምንጮችን ከሃገራዊና ማህበረሰባዊ እውነታዎች ጋር አጣምሮ በማጥናት ተግዳሮቶችን በመለየትና መፍትሔዎችን በመጠቆም ረገድ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ቀዳሚውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡

በኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ያለዉን የሸሪዓ ሕግ ትምህርት አቀራረብ ስናይ አማራጭ የትምህርት ዓይነት *(elective Course)* በመሆን ለቅድመ-ምረቃ የሕግ ተማሪዎች ይሰጣል፡፡ የሸሪዓ የፍትሕ ሥርዓቱን *ኡሱል* እና *ፊቅሕ* ጥናቶች በሰለጠኑ ባለሙያዎች ይመራ ዘንድ እንዲሁም የወለድ-ነጻ የባንክ ቁጥጥሩ እና አገልግሎቱ በሰለጠነ የሰው ኃይል መራመድ ይችል ዘንድ ከጀርባ ያለው የሃገራችን የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓት ተፈላጊዉን ብቁ ባሙያዎች ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ በሕግ ትምህርት መስክ የሚሰጠው የሸሪዓ ሕግ ትምህርት በይዘቱም ሆነ በአቀራረቡ መሠረታዊ ማሻሻያ ሊደግርበት ይገባል፡፡ ሦስተኛው ሸሪዓ ምንጭ የሆነውን እና ለዝርዝር የቤተሰብና የፋይናንስ ሕጎች መሠረት የሆነው *ኡሱል አል-ፊቅሕ (Islamic Jurisprudence)* እውቀት ዘርፍ ራሱን ችሎ ሊቀርብ ይገባል፡፡ የሸሪዓ ኢስላማዊ የግልና የቤተሰብ ሕግ *(Islamic Personal and Family Law)* እና የፋይናንስ ዝርዝር ሕጎች ጥናት *(ፊቅሕ)*

---

[77] አብዱልዋሴ ዩሱፍ፣ *የሸሪዓ ሕግ አፈጻጸም በኢትዮጵያ፡- የሸሪዓ ሕግን አስመልክቶ የተደረገ ውይይት ቃለ-ጉባኤ* ወንበር፡- የዓለማየሁ ኃይሌ መታሰቢያ ድርጅት ቡሌቲን፣ 18ኛ መንፈቅ፣ 64-65 (2009 ዓ.ም).

[78] KAMALI, SHARIA LAW, ግርጌ ማስታወሻ 8, pp. 175, 237 & 253.

[79] Directives to Authorize the Business of Interest Free Banking, Directive Number SBB/51/2011.

*(Islamic Finance and Banking Law)* ደግሞ ከሑሱል ጥናት ተነጥሎ ለብቻው የሚሰጥበት የትምህርት ቀረጻ የቅድመ-ምረቃ የሕግ ትምህርት ሥርዓት አካል ቢደረግ በዘርፉ በተጨባጭ እያጋጠሙ ያሉ የብቃትና የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ችግሮችን ማቃለል ይቻላል፡፡

* * * * *